# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ 81ኛ ዓመት ቁጥር 326 ሐምሌ 26 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# ለግብርና ዘርፉ በተሰጠው ትኩረት ተጨባጭ ውጤት እየተመዘገበ መሆኑ ተገለጸ

**ስምስም መንግሥቱ**

አዳማ፡- መንግሥት ለግብርናው ዘርፍ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ በመሥራቱ በዘርፉ ተጨባጭ ውጤት እየተመዘገበ መሆኑን የፕላን ሚኒስቴር ገለፀ፡፡

የፕላን ሚኒስትሯ ዶክተር ፍጹም አሰፋ፣ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሰሞኑን በአዳማ ከተማ ባዘጋጀው ሰባተኛው ስለኢትዮጵያ የፎቶግራፍ አውደርዕይና የፓናል ውይይት ላይ እንደተናገሩት፣ የግብርናው ዘርፍ ላይ የሚደረገው ኢንቨስትመንት ድህነትን በመቀነስ ላቅ ያለ ሚና አለው፡፡

ግብርና ላይ የሚደረገው ኢንቨስትመንት ድጋፍ ከሚጠበቀው በላይ ውጤት የሚያስገኝ በመሆኑ መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ይገኛል ያሉት ዶክተር ፍጹም፣ አንዳንድ ክፍተቶች ቢኖሩም ባለፉት ሶስትና አራት ዓመታት የተሠሩት ሥራዎች በተለያየ መልክ የሚገለጽ ውጤት የተገኘባቸው ናቸው ብለዋል፡፡

መንግሥት ግብርናውን በማዘመን ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር ከትራክተር ጀምሮ አነስተኛ የግብርና የግብዓት መሣሪያዎች ከውጭ ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ ለመካናይዜሽን የተሰጠውን ትኩረት አንዱ ማሳያና ትልቅ ውሳኔ እንደሆነ ያስረዱት ዶክተር ፍጹም፣ በአሁኑ ጊዜም በሀገር ደረጃ እየተከናወነ ባለው የግብርና ሥራ ግብዓቱ እየዋለ መሆኑንና 30 በመቶ የሚሆነው

ለግብርና ዘርፉ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - ዳኜ አበራ

ዶክተር ፍጹም አሰፋ













አቶ ተስፋዬ ንዋይ

# የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ያለባቸውን የመዝገብ ጫና ለማቃለል መደበኛ ሥራቸውን ለአንድ ወር አራዘሙ

## - ለ177 ለሚጠጉ ጉዳዮች እልባት መስጠቱም ተጠቁሟል

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ያለባቸውን የመዝገብ ጫና በማቃለል ወደ 2015 ዓ.ም የሚያልፉ መዝገቦችን ቁጥር ለመቀነስ በማሰብ መደበኛ ሥራቸውን እያከናወኑ እስከ ነሐሴ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ እንዲቆዩ ተወሰነ፡፡ ፍርድ ቤቶቹ በ2014 በጀት ዓመት ለ176 ሺህ 797 ጉዳዮች እልባት መስጠቱንም አስታውቋል፡፡

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ‹‹የትግራይ ሕዝብ የሕወሓት መሪዎችን የጦርነት ቅስቀሳ ሊያወግዝ ይገባል››

-ኮሎኔል ፍስሐ ገብረመድህን

የትዴፓ የፀጥታና ደህንነት ጉዳዮች ኃላፊ

**መኣርግ ገ/እግዚኣብሔር**

አዲስ አበባ፡- የሕወሓት መሪዎች የትግራይን ሕዝብ እንደገና ወደ ከፋ ችግር ውስጥ ለመክተት ‹‹ሶስተኛ ዘመቻ›› በሚል የሚያደርጉትን የጦርነት ዘመቻ የትግራይ ሕዝብ በፅኑ ሊያወግዘው ይገባል ሲሉ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ትዴፓ) የፀጥታና ደህንነት ጉዳዮች ኃላፊ ኮሎኔል ፍስሐ ገብረመድህን ገለጹ።

ኮሎኔል ፍስሐ ከወጋህታ ጋዜጣ ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደገለጹት፣ የሕወሓት መሪዎች ‹‹ሦስተኛ ዘመቻ›› በሚል ስም የጦርነት ዘመቻ እያካሄዱ ይገኛሉ፣ ይህ ወደ ጦርነት የሚያመራ ከሆነ በሀገሪቱ በተለይም በትግራይ ሕዝብ ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ ከባድ ነው።

እንደ ኮሎኔል ፍስሐ ገለጻ፣ ከሰላም እንጂ ከጦርነት የሚገኝ ጥቅም የለም፣ ጦርነት የሰውን ሕይወት፣ አካል፣ ሀብት ይበላል። ለልማት ሊውል የሚገባው የሕዝብ ገንዘብ ለጦርነት ሲውል ትልቅ ኪሳራ ነው። በሀገሪቱ ሀብት በተገዛ መሣሪያ የሀገሪቱን መሠረተ ልማት ከማውደምም በተጨማሪ አምራች ወጣት ሕይወቱ ሲጠፋና አካሉ ሲጎዳ ኪሳራው በጣም ከባድ ነው፡፡

የትግራይ ሕዝብ ችግሩ በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ ነው ፍላጎቱ፣ ይሁን እንጂ የሕወሓት መሪዎች ችግሩ በጦርነት እንፈታዋለን በሚል ሁሉም ወጣት መታጠቅ



ወይም ትግሉን መቀላቀል አለበት በሚል እሳቤ የጦርነት ዘመቻ እያካሄዱ እንደሆኑ ነው ኮሎኔል ፍስሐ የሚገልፁት።

የሕወሓት መሪዎች ለግል ጥቅማቸው ሲሉ በትግሉ ያልተሳተፈ ምንም አይነት ጥቅም አያገኝም በማለት

‹‹የትግራይ ሕዝብ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ከ69 ሚሊዮን ዶላር በላይ ወጪ የተደረገበት ወደብ ሥራ ሊጀምር ነው

**ውብሸት ሰንደቁ**

ድሬዳዋ፡- ከ69 ሚሊዮን ዶላር በላይ በሆነ ወጪ እየተገነባ የሚገኘው የድሬዳዋ ደረቅ ወደብና ተርሚናል በነሐሴ ወር መጨረሻ ሥራ እንደሚጀምር የድሬደዋ ደረቅ ወደብና ተርሚናል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ገለጸ፡፡

የድሬደዋ ደረቅ ወደብና ተርሚናል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ወይዘሮ እመቤት ፍሰሐ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፣ ከ69 ሚሊየን ዶላር በላይ በሆነ ወጪ እየተገነባ የሚገኘው የድሬዳዋ ደረቅ ወደብና ተርሚናል ግንባታ 98 በመቶ ተጠናቋል፡፡ የቢሮ መሣሪያዎች እና ልዩ ልዩ ግብዓቶች እየቀረቡ ነው፡፡ ቀሪ ሥራዎችም በፍጥነት ተከናውነው ወደቡ በነሐሴ ወር መጨረሻ ላይ ሥራ ይጀምራል፡፡

ሁሉም የፕሮጀክቱ ሥራዎች በታቀደላቸው ጊዜ

ከ69 ሚሊዮን ዶላር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







# የክልሉ የመንገድ ሽፋን ከ58 ሺህ ኪሎሜትር በላይ መድረሱ ተነገረ

**ፍቃዱ ዴሬሳ**


ኢንጂነር ሄለን ታምሩ

አዲስ አበባ፡- በ2014 ዓ.ም የኦሮሚያ ክልል መንገድ ሽፋን 58 ሺህ 945 ኪሎሜትር መድረሱን የክልሉ መንገድና ሎጂስቲክ ቢሮ አስታወቀ፡፡ ክልሉ በቀጣይ ዓመት በተለያየ ምክንያት ያልተጠናቀቁ የመንገድ ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ ላይ ትኩረት አድርጎ እንደሚሠራም አስታውቋል፡፡

የክልሉ መንገድና ሎጀስቲክስ ቢሮ ኃላፊ ኢንጂነር ሄለን ታምሩ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት እስከ 2013 ዓ.ም ድረስ የክልሉ መንገድ ሽፋን 58ሺህ ኪሎሜትር የነበረ ሲሆን በ2014 ዓ.ም የአስፋልትና የጠጠር መንገዶችን ጨምሮ ከ58 ሺህ 945 ኪሎሜትር በላይ ደርሷል፡፡

በመንገድ ዘርፍ በባለፈው ዓመት ክልሉ በመደበው በጀት 245 ኪ.ሜ ለመገንባት በማቀድ 128 ነጥብ 68 ኪ.ሜ መገንባቱን አንስተው፣ በዞን ደረጃ ደግሞ 306 ኪ.ሜ መገንባት መቻሉን ተናግረዋል፡፡ በክልል ደረጃ ከታቀደው እቅድ ባነሰ መልኩ መፈፀሙ በክልሉ በተለያዩ አካባቢዎች በተለይም በምዕራብ ኦሮሚያና ጉጂ አካባቢዎች የሚስተዋሉ የፀጥታ ችግሮች ዋነኛ ምክንያቶች ናቸው ብለዋል፡፡

የገጠር መንገድ ተደራሽነት በዞን ደረጃ የሚገነባ ሲሆን በዚህ ረገድም 151 መንገዶች ለመገንባት ታቅደው 121 መጠናቀቃቸውንና የተገነቡ መንገዶችም በአጠቃላይ ከሁለት ሺህ ኪሎሜትር በላይ እንደሚያካልሉ ተናግረዋል፡፡

በክልሉ በጀት ለመገንባት ከታቀዱ 36 ድልድዮች መካከል 25ቱ ተገንብተው ለኅብረተሰቡ አገልግሎት መስጠት መቻላቸውንም አስታውቀዋል፡፡ በዞን ደረጃ ለመገንባት ከታቀዱ 60 ድልድዮች መካከል 42 የሚደርሱት መጠናቀቃቸውን የገለፁት ኢንጂነር ሄለን፣ በክልሉ በአጠቃላይ 67 ድልድዮች በዓመቱ ተገንብተው መጠናቀቃቸውን አንስተዋል፡፡ በቀጣይ ዓመትም 35 ድልድዮችን ገንብቶ ለማኅበረሰቡ ክፍት እንደሚያደርግም ቢሮው አስታውቋል፡፡

እንደ ኢንጂነር ሄለን ገለፃ፣ በክልሉ መንግሥት ለመንገድና ሎጀስቲክስ ዘርፎች ስድስት ቢሊዮን ብር በጀት የተያዘ ሲሆን በጀቱን በአግባቡና በኃላፊነት ከመጠቀም አኳያም ቢሮው በትኩረት ሲሠራ ቆይቷል፡፡

ከመንገዶች የእድሳት ጥራት ጋር በተያያዘ በርካታ ጥያቄዎች የሚነሱበት ቢሆንም በዚህ በጀት ዓመት 6659 ኪሎሜትር መንገድ የተጠገነ መሆኑን አንስተዋል፡፡ 3210 ኪሎሜትር ደግሞ በገጠር መንገድ የተጠገነ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በሎጀስቲኩ ዘርፉ በክልሉ የተቀናጀ የተሽከርካሪ መናኸሪያዎችን መገንባት ሲሆን በዚህም በበጀት ዓመቱ አምስት የሚደርሱ ፕሮጀክቶችን ለመገንባት ታቅዶ 60 በመቶ የሚደርሰው መጠናቀቁን ገልፀዋል፡፡

በ2015 ዓ.ም የመንገድ ግንባታውን ችግር ለመፍታትና የማኅበረሰቡን የመንገድ ግንባታ ጥያቄ ደረጃ በደረጃ ለመፍታት 5ነጥብ2 ቢሊዮን ብር በጀት መያዙን የጠቆሙት ኃላፊዋ፣ በቀጣይ ዓመት ተጀምረው ያልተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ላይ ትኩረት እንደሚደረግ ገልፀዋል፡፡

በፀጥታ ችግር ምክንያት በ2014 ዓ.ም ያልተጠናቀቁ ፕሮጀክቶችን የማጠናቀቅ ተግባር እንደሚከናወንና በዚህም 213 ኪሎሜትር የሚደርስ መንገድ ተሰርቶ ለማኅበረሰቡ ክፍት እንደሚሆን አስታውቀዋል፡፡

ከዚህም ባሻገር የክልሉን የገጠር መንገድ ተደራሽነትን እውን ለማድረግ በተያዘው እቅድ በ2015 በጀት ዓመት 1935 ኪሎሜትር መንገድ በመገንባት የማኅበረሰቡን የመንገድ ጥያቄ ለመመለስ ቢሮው የሚተጋ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

6659 ኪሎሜትር በፌዴራሉ መንግሥት፣ 6849 ኪሎሜትር ደግሞ በክልሉ መንግሥት የተበላሹ መንገዶች የሚጠገኑ መሆኑን አመልክተው፣ እንደ ክልሉ የቆዳ ስፋት ሲታይ ይህ በቂ ባለመሆኑ በቀጣይ ዓመታት ለዘርፉ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡



ፎቶ - ሃዲስ አብርሃ

# ዓመታዊ የመጽሐፍት አውደ ርዕይና የሥነ ጽሑፍ ሽልማት ሊካሄድ ነው

**ፍቃዱ ዴሬሳ**

አዲስ አበባ፡- ንባብ ለሕይወት ኢትዮጵያ ፕሮጀክት ከኢትዮጵያ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት አገልግሎት ጋር በመተባበር ዓመታዊ የመጽሐፍትና የትምህርት ተቋማት አውደ ርዕይ እንዲሁም የሥነ ጽሑፍ ሽልማት ሊዘጋጅ መሆኑ ተነገሯል፡፡

ከሐሙስ ሐምሌ 28 እስከ ነሐሴ 22/2014 ዓ.ም የሚቆየውን አውደ ርዕይ በማስመልከት በጋራ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥተዋል።

የኢትዮጵያ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር አቶ ዩኩኖአምላክ መዝገቡ በመግለጫው እንዳስታወቁት ንባብ ለሕይወት መርሐ ግብር ለበርካታ ዓመታት የክረምት ወቅት ሲከናወን የቆየ መርሐ ግብር መሆኑን ገልፀው፣ በዚህ ዓመት ሰፋ ባለ መልኩ የመጽሐፍት አውደ ርዕይ፣ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እንዲሁም በንባብና በትምህርት ዘርፍ ላይ የተሠማሩ ተቋማት የሚሳተፉበት ፕሮግራም ነው፡፡

በዚህ አውደ ርዕይ ወላጆች ሕጻናትን አውደ ርዕይ ወደሚዘጋጅበት ስፍራ ይዞ በመምጣት የንባብ ባህላቸውን እንዲያዳብሩና እንዲያጎለብቱ ማድረግ ይጠበቅበታል ብለዋል፡፡

በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል በሚያዘጋጀው ፕሮግራም በርካታ መጽሐፍቶች ቀርበው በተሻለ ዋጋና አማራጭ ለሽያጭ የሚቀርቡበት መሆኑን የንባብ ለሕይወት ኢትዮጵያ ፕሮጀክት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር ወ/ሮ ኤሚ እንግዳ ተናግረዋል።

ለአምስተኛ ጊዜ ለሚካሄደው አውደ ርዕይ ሁሉም የማኅበረሰብ ክፍል በነፃ የተጋበዘ በመሆኑ ወላጆች ልጆቻቸውን በስፍራው ይዘው በመገኘት ወላጆች አርዓያ በመሆን ሕፃናት የንባብ ልምዳቸውን እንዲያዳብሩና አንባቢ ትውልድ ለመፍጠር በሚደረገው እንቅስቃሴ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ሊወጡ ይገባል ብለዋል።

በአውደ ርዕዩ አሳታሚዎች፣ ደራሲያን፣ የምርምር ተቋማት፣ ጸሐፊዎች፣ የመጽሐፍት አከፋፋዮች እንዲሁም አንባቢዎች የሚገናኙበት መድረክ መሆኑን ጠቅሰው፣ ያላነበበ ትውልድ ለራሱም ሆነ ለሀገሩ የሚጎለው ነገር በመኖሩ የሚያነብ ትውልድ በመፍጠር እራሱንና ሀገሩን የሚለውጥ ትውልድ መፍጠር እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡

በሌላ በኩል የዚህ መርሐ ግብር አካል የሆነው አራተኛው የሆሄ የሥነ ጽሑፍ ሽልማት "መጽሐፍት ለእውቀት ዳበራ! ለጥበብ ጎታ!" በሚል መሪ ቃል ነሐሴ 30/2014 ዓ.ም በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት የቲያትርና ባህል አዳራሽ እንደሚካሄድም ተገልጿል፡፡

የሆሄ የሥነ ጽሑፍ ሽልማት ዋና ዳይሬክተር አቶ አፍሬም ብርሃኑ እንደገለፁት በ2011 ዓ.ም የታተሙ ምርጥ የዓመቱ መጽሐፍት በረዥም ልብ ወለድ፣ አጭር ልብ ወለድ፣ ግለታሪክ፣ በልጆች መጽሐፍት ዘርፍ፣ ግጥምና ጥናትና ምርምርን ጨምሮ በስድስት የመጽሐፍት ዘርፎች እንዲሁም የሕይወት ዘመን የሥነ ጽሑፍ ባለውለታና ለንባብ መዳበር አበርክቶ ያደረጉ ግለሰቦችና ተቋማት በአጠቃላይ ለአስር ዘርፎች ሽልማት እንደሚሰጥ ተናግረዋል፡፡

እንደ አቶ አፍሬም ገለፃ በሁሉም ዘርፎች አንደኛ የሚወጡ መጽሐፍት የዓመቱ ምርጥ መጸሐፍ ሽልማት አሸናፊዎች ይሆናሉ፡፡ ይህንንም የመለየት ሂደት ከአንባቢያን የሚሰጥ ድምፅ ከ20 በመቶ የሚይዝ ሲሆን ዳኞች በዳግም ግምገማ 80 በመቶ ውጤት በመስጠት ይሆናል፡፡

# የላይኛው አዋሽ ተፋሰስ
## አካባቢን በዓለም ቅርስነት ለማስመዝገብ ጥያቄ ቀረበ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**


ረዳት ፕሮፌሰር አበባው አያሌው

አዲስ አበባ፡- የላይኛው አዋሽ ተፋሰስ አካባቢን በዓለም ቅርስነት ለማስመዝገብ ጥያቄ መቅረቡን የኢትዮጵያ ቅርስ ጥበቃ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ረዳት ፕሮፌሰር አበባው አያሌው አስታወቁ።

ኢትዮጵያ በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና ባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) በዓለም ቅርሶች መዝገብ በርካታ የማይዳሰሱ እና የሚዳሰሱ ቅርሶችን አስመዝግባለች።

ከቅርሶቹም መካከል የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት፣ የሠሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ፣ የፋሲል ግንብ፣ አክሱም፣ የሐረር ጀጎል ጥንታዊ ከተማ፣ የጢያ ትክል ድንጋይ ይገኙበታል።

በተጨማሪ የታችኛው አዋሽ ሸለቆ፣ የታችኛው ኦሞ ሸለቆ የአርኪኦሎጂ ስፍራ፣ የኮንሶ መልክዓ ምድር፣ የመስቀል በዓል አከባበር፣ የሲዳማ ሕዝብ ዘመን መለወጫ ፍቼ ጫምባላላ፣ የገዳ ሥርዓት እና የጥምቀት በዓል አከባበር ተካተውበታል።

የኢትዮጵያ ቅርስ ጥበቃ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ረዳት ፕሮፌሰር አበባው ለኢዜአ እንዳሉት፥ በርካታ የኢትዮጵያ ቅርሶች በዓለም ቅርስነት የተመዘገቡ ሲሆን፤ አሁን ላይ የላይኛውን የአዋሽ ተፋሰስ አካባቢን ለማስመዝገብ ጥያቄ መቅረቡን ተናግረዋል።

የላይኛው አዋሽ ተፋሰስ "ሆሞ ሃቢሊስ" የተባለው የጥንት የሰው ልጅ ዝርያ ሲጠቀምባቸው የነበሩ ጥንታዊ የድንጋይ መሣሪያዎችን የያዘ አካባቢ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

በዚህም የላይኛውን አዋሽ ተፋሰስ በዩኔስኮ እንዲመዘገብ ጥያቄ መቅረቡን እና ዝርዝር እጩዎች ውስጥ መካተቱን ጠቅሰው ፥ ከዚህ አኳያ አካባቢውን የሚመለከቱ መረጃዎችን የማደራጀት ሥራ እየተከናወነ እንደሚገኝ አብራርተዋል፡፡

ከኢትዮጵያ ካርታ ሥራዎች ድርጅት ጋር በመሆን የአካባቢውን ካርታ ለማዘጋጀት እንደሚሠራም ጠቁመዋል፡፡

የመልካ ቁንጡሬ ቅድመ ታሪክ መካነ ቅርስ ሙዚየም ኃላፊ አቶ ተስፋዬ ተሰማ በበኩላቸው መልካ ቁንጡሬ በላይኛው አዋሽ ተፋሰስ ውስጥ የሚገኙ የቅድመ ታሪክ ቦታዎች ስብስብ የያዘ ሙዚየምና የምርምር ስፍራ መሆኑን አብራርተዋል።

አካባቢው ከአዲስ አበባ በስተደቡብ 50 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን ፥ የ1 ነጥብ 8 ሚሊዮን ዓመት እድሜ ያላቸው ጥንታዊ ቅርሶች መገኛ ነው፡፡

ላለፉት 52 ዓመታት የጥናትና ምርምር ቦታ እንዲሁም የቱሪስት መዳረሻ ሆኖ እያገለገለ እንደሚገኝም ነው ያነሱት፡፡



ፎቶ፡- ገባቦ ገብሬ

ረዳት ፕሮፌሰር ግዛቸው አንዳርጌ

# ተቋሙ ጥቁር ደም የተሰኘውን ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ለማስቀረት ፕሮጀክት ቀርጾ እየሠራ ነው

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል በብዛት የሚስተዋለውን ጥቁር ደም የተሰኘውን ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ለማስቀረት የሁለት ዓመት ፕሮጀክት ቀርጾ እየሠራ መሆኑን በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የሐዲስ ዓለማየሁ ባህል ጥናት ተቋም ገለጸ።

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የሐዲስ ዓለማየሁ የባህል ጥናት ተቋም ዳይሬክተር ረዳት ፕሮፌሰር ግዛቸው አንዳርጌ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ደም መመላለስ በአማራ ክልል በተለይም በምሥራቅ ጎጃም ዞን በበርካታ ወረዳዎች በስፋት የሚስተዋል ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ነው። በመሆኑም ዩኒቨርሲቲው ይህንን ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ለመቅረፍ ችግሩ ጎልቶ በሚስተዋልበት በምሥራቅ ጎጃም ዞን ሸበል በረንታ ወረዳ የሁለት ዓመት ፕሮጀክት ቀርጾ እየሠራ መሆኑን አስታውቀዋል።

በደም መመላለስ በድርጊቱ ላይ እጃቸው የሌለ፣ ያልመከሩና ያልዘከሩ ሰዎች የደም መመለሻ እየተደረጉ ሕጻናት ያለአሳዳጊ፣ አረጋውያን ያለ ነዋሪ ቀርተዋል፤ ብዙዎች ቀያቸውን ለቀው ስለሚሰደዱ ለልማት መዋል ያለበት መሬትም ጾም ያድራል ያሉት ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ የችግሩ ሰለባዎች የደህንነት ስጋት ስላለባቸው ገበያን ጨምሮ በሌሎችም ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ አይሳተፉም። ይህም ከፍተኛ የሆነ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ እየፈጠረ በመሆኑ በወረዳው ያለውን ችግር ለመቅረፍ ዩኒቨርሲቲው በሐዲስ ዓለማየሁ የባህል ጥናት ተቋም በኩል የሁለት ዓመት ፕሮጀክት ቀርጾ እየሠራ ነው ብለዋል።

ሸበል በረንታ ወረዳ በኢትዮጵያ ታሪክ ከፍታ ላይ ያለና ሀገር ጭንቅ ውስጥ በምትወድቅበት ወቅት ሁሉ ግንባር ቀደም ተጋድሎ በማድረግ ዳር ድንበሯን ለመጠበቅ ያበረከተው አስተዋጽኦ ከፍ ያለ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ የደም መመላለስ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ግን የአካባቢውን ድንቅ ታሪክ እየደመሰሰ በመጥፎ ታሪክ እየለወጠ ነው። በመሆኑም ዩኒቨርሲቲው ለሰላም እሴት ግንባታ ግንባር ቀደም ሚና መጫወት ስላለበት በሐዲስ ዓለማየሁ የባህል ጥናት ተቋም አማካኝነት ጠንካራ ባህሎች እንዲቀጥሉና ለትውልድ እንዲተላለፉ፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ደግሞ እንዲቀረፉ ለማድረግ ይሠራል።

ሥራው ሲጀመር የችግሩን ስፋትና ጥልቀት ለመረዳት ጥረት መደረጉን ጠቁመው፤ ከባህል፣ ከሰላምና ደህንነትና ከፖሊስ አካላት ጋር በመተባበር በተሠራው ሥራ የተሻለ ውጤት መገኘቱን ተናግረዋል።

ደም አድራቂ ሽማግሌዎችን ከአገር ሽማግሌ፣ ከሃይማኖት አባቶችና ከወጣት በመምረጥ 59 የሚደርሱ እርቆች እንዲፈጸሙ ተደርጓል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በዚህ መልኩ መቃቃሮችን ማስወገድና አብሮነትን ማስቀጠል ሲቻል ትኩረቱን ሁሉ ልማት ላይ ማድረግ ይቻላል ብለዋል።

በርካታ ወረዳዎች ሸበል በረንታ ላይ ተሞክሮ የተሻለ ውጤት ያስገኘውን በእርቅ ደም የማድረቅ ሥራ ላይ ያለውን ተሞክሮ እንዲያሰፋ እየጠየቁ መሆኑን ጠቅሰው፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሥራውን በክልል ብሎም በአገር ደረጃ የሚስተዋሉ ችግሮችን መፍታት የሚችልበትን ሁኔታ ለመፍጠር እንደሚሠራ ገልጸዋል።

# "ስለኢትዮጵያ"- በተሳታፊዎች አንደበት

**ስምስም መንግሥቱ**



አንዳንዶች በተመስጦ፣አንዳንዶች ደግሞ በአግራሞት፣ ይሄም አለ?በሚል አስተያየት ነበር የተዘጋጀውን የፎቶግራፍ ዐውደ ርዕይ ሲጎበኙ ያስተዋልኩት። የፎቶግራፍ ዐውደ ርዕይው የኋላውንም፣ የቅርቡንም፣ አሁን የምንገኝበትንም የማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎችን የሚያስቃኝ በመሆኑ የአብዛኛውን ጎብኝ ቀልብ የገዛ ነበር ማለት ይቻላል። ‹‹ከሺህ ቃላት አንድ ፎቶ›› ይባል የለ ከነአባባሉ፤ የሚናገሩ ፎቶዎችን በማየት ብቻ ታሪክን ወደኋላም ወደፊትም ያስታወሱ ሰዎችም አልጠፉም። እንዲህ የተለያየ ስሜት ያለው ጎብኝ የተገኘው 82 ዓመት ከአንድ ወር ያለፈው አንጋፋው የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በአዳማ ከተማ ስለኢትዮጵያ በሚል ባዘጋጀው የፎቶግራፍ ዐውደ ርዕይና የፓናል ውይይት ላይ ነበር።

ከፎቶግራፍ ዐውደ ርዕይው ጎብኝዎችና ከፓናሉ ተሳታፊዎች መካከል በአዳማ ከተማ ነዋሪ የሆኑት ሀደ ሲንቄ ቱለማ ወይዘሮ አፀዱ ቶላ አንዷ ነበሩ። እርሳቸውም‹‹የፎቶግራፍ ዐውደ ርዕይው የቀደመውን ወይንም ያለፍንበትን ታሪክ፣አሁን ላይ የደረስንበትንና የምንገኝበትን ለውጥ አሳይቶናል። የኋላውን ካስታወስን በኋላ ደግሞ አሁን ሀገራችን በለውጥ ጎዳና ላይ የምትገኝ በመሆኑ ምን ማድረግ እንዳለብን ወደሚለው ነገር ያመጣናል። ›› በማለት ነው አስተያየታቸውን የሰጡን።

ሀደሲንቄ ቱለማ ወይዘሮ አፀዱ አሁን ላይ አንድነት፣ ፍቅር፣ መተባበር፣ መመካከር፣ ለሀገር ማሰብ ያስፈልጋል። መከፋፈል አያዋጣም። አንድ ከሆን ሀገራችንን እናሻግራለን። ወልደን እንስማለን። ዘርተን እንቅማለን ሀገራችንን እንጦርበታለን። ሌላ ሀገር የለንም። ኑሮአቸውን በውጭ ሀገር አድርገው ተደላድለው ተቀምጠው ወደ ኢትዮጵያ መጥፎ የሆነውን ነገር የሚነዙት ለኢትዮጵያውያን አይጠቅምም። ከኢትዮጵያውያን ጋር ችግሩንም ጥሩውንም እየተካፈሉ የሚያስተዳድሩንን መሪዎቻችንን ክብር እንሰጣቸዋለን። መከበርና መመስገን አለባቸው። እየሠሩ ያለው ሥራ ትልቅ ነው። ለውጥም እያመጡ መሆኑን እያየን ነው። ከሕዝቡ የሚጠበቀው አንድ መሆንና እነርሱን መርዳት ነው። ሰላም መፍጠር የሚጠበቀው ከመንግሥት ብቻ አይደለም። ከሕዝብም ይጠበቃል። ሁሉም ተነጋግሮና ተመካክሮ ሀገሩን ማሻገር ይጠበቅበታል ሲሉም ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በፎቶግራፍ ሰንዶ ያስቀመጠውን ታሪክ በተመለከተም ወይዘሮ አፀዱ ‹‹መንግሥት ይለወጣል። ሁሉም ነገርም ያልፋል። ታሪክ ግን ይቀመጣል። ይሄ ደግሞ መሆን ያለበትና ትውልድም እንዲያውቀው መደረግ አለበት። ታሪክ በመኖሩ ነው ወደኋላ መለስ ብለን ያስታወስነው። የሀገር ትውስታና ለውጥንም የሚያሳይ በመሆኑ ትልቅ ቦታ ይሰጠዋል›› በማለት ሊበረታታና በመንግሥትም ሊደገፍ እንደሚገባ ገልጸዋል። በተለይም ወጣቱ ትውልድ ሁሉም ነገር አላፊ መሆኑን ተገንዝቦ ለሀገሩ ዘብ መቆም አለበት ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ሌላው አስተያየታቸውን የሰጡን የፊንፊኔ ንግድ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ኤልያስ ጉዮ ናቸው። የፎቶግራፍ አውደ ርዕይው የቀደመውንም የአሁኑንም የልማት እንቅስቃሴ ያዩበት እንደሆነና መደሰታቸውንም ነው የገለጹት። አቶ ኤልያስ፤የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የፓናል ውይይትን ባቀናጀ የፎቶግራፍ ዐውደ ርዕይ ዝግጅቱን በአዳማ ላይ በማቅረብ ብቻ መወሰን የለበትም ይላሉ። በመላ ኢትዮጵያ ውስጥ ቢካሄድ ከፍ ያለ ግንዛቤና ትምህርት ይሰጣል ብለው ያምናሉ።

‹‹ኢሕአዴግ የደርግ መንግሥትን ጥሎ ሀገሪቱን ሲረከብ በሽግግሩ ወቅት እኔ የኦሮሚያ ክልል ሥራ አስፈጻሚ ነበርኩ" ያሉት አቶ ኤልያስ፤ ኢሕአዴግ በሥልጣን በቆየባቸው ዓመታት ስለዘርና ጎሳ ነበር በሕዝብ ውስጥ ሲዘራ የነበረው ብለዋል። በብዙ ወጣቶች ውስጥ የቀረውም ይኸው ነው። ይህን መጥፎ ዘር ከጭንቅላት ውስጥ ለማውጣት ተደጋጋሚ ጥረቶችን ይጠይቃል። በመሆኑም የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የጀመረውን ስለኢትዮጵያ በሀገሪቱ በመዞር ኢትዮጵያ ከየት ተነስታ የት እንደደረሰች ለማሳወቅ እንቅስቃሴውን ቢያጠናክር ደስ ይለኛል ሲሉም ሀሳባቸውን ሰጥተዋል።

ዝግጅቱ ወጣቶችን የሚያሳትፍ ቢሆን የተሻለ እንደሆነ የጠቆሙት አቶ ኤሊያስ፤በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኙ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎችን ለውይይት ጋብዞ ሀሳብ እንዲንሸራሸር ማድረጉንም አድንቀዋል። በፎቶግራፍ ዐውደርዕይው ላይ የክልሎች ምስረታን የሚያሳይ ነገር አለማግኘታቸውንና ቢካተት ጥሩ እንደነበር ገልጸዋል። ታሪክን ሰንዶ አለማስቀመጥ ትልቁ ክፍተት መሆኑን የጠቆሙት አቶ ኤልያስ ታሪክ ሰንዶ የማስቀመጥ ባህል ባለመዳበሩ ሁሉም በፈለገው መንገድ ታሪክን እንዲናገርና ተጨባጭ የሌለው ነገር እንዲያቀርብ መንገድ እንደከፈተና ባልተሰነደ ታሪክ ዜጎች ሲረበሹ መቆየታቸውንም ጠቁመዋል። ከዚህ አኳያ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ኃላፊነቱን እየተወጣ እንደሆነ አመልክተዋል።

የፎቶግራፍ ዐውደ ርዕይው በጣም የሚያሳዝንና የሚያስደስት ነገሮችን ለማየት ዕድል እንደሰጣቸው የነገሩን የታዳሽ ስቲል አምራች ድርጅት ባለቤትና ዳይሬክተር ዋና ኃላፊ አቶ ክቡር ይስፋ ተክሌ በበኩላቸው፤እንዲህ ያሉ ሲምፖዝየሞች መነቃቃትን ይፈጥራሉ ብለዋል። ጦርነት ቦታ ላልተገኘ፣በጦርነቱም የደረሱ ማኅበራዊ፣ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ቀውሶች ላይ ሰው ተቋሙ በፎቶግራፍ ሰንዶ ሌላው እንዲያየው ማድረጉ ያስመሰግነዋል ብለዋል። የሚወራውንና በተግባር ያለውን እውነታ የሚያሳይ መሆኑንና ለብዙኃን መቅረብ ያለበት ጥሩ መረጃ ሰጪ እንደሆነ አመልክተዋል። በኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ የተደረገው ውይይትም ለሀገር ኢኮኖሚ እድገት ጠቃሚ እንደሆነም ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በጅግጅጋ፣ ድሬዳዋ፣ ሐረር፣ሐዋሳ፣አርባምንጭ፣ጅማ ከተሞች ቀድሞ ያካሄደ ሲሆን፣ባለፈው ሳምንት ደግሞ ሰባተኛውን መድረክ በአዳማ አካሂዷል። የፓናል ውይይቱም የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ላይ ትኩረት ያደረገ ነበር።

# የዲፕሎማሲውን መሻሻል ለማስቀጠል መንግሥት ለሰላም ያለውን ቁርጠኝነት በአግባቡ ማሳየት እንደሚገባ ተገለጸ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- አሁን በዲፕሎማሲው መስክ የታየውን መሻሻል ወደተሻለ ደረጃ ለማሳደግና ለማስቀጠል መንግሥት ከሕወሓት ጋር ያለው ጦርነት በውይይት እንዲፈታና ለትግራይ ሕዝብም የሰብዓዊ ርዳታዎች በአግባቡ እንዲደርስ የወሰዳቸውን ተከታታይ ርምጃዎች ለተለያዩ ሀገራት እና ድርጅቶች ማሳወቅ እንደሚገባ ተገለጸ።

በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህርና ተመራማሪ አቶ ሱራፌል ጌታሁን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ለትግራይ ክልል እርዳታ ያለ ምንም ገደብ እንዲደርስ መደረጉ እና ሌሎች የሰላም አማራጮች መወሰዳቸው ምዕራባውያንና ተቋሞቻቸው ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ያላቸውን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እንዲያሻሽሉ አስችሏል።

አቶ ሱራፌል እንደገለጹት፤ በሰሜን የሀገራችን ክፍል በነበረው ጦርነት ምዕራባውያን በኢትዮጵያ ላይ የተንሻፈፈ አቋም ነበራቸው። በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ ዲፕሎማሲያዊ ጫና ሲፈጥሩም ቆይተዋል። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፣ የአውሮፓ ኅብረትና የመሳሰሉት ተቋሞቻቸው የኢትዮጵያን መንግሥት የመክሰስና የሽብር ቡድኑን የመደገፍ ዝንባሌ አሳይተዋል። ቀደም ሲል በተለያየ ጊዜ ያወጧቸው መግለጫዎች አድሎአዊና መንግሥትንም ጫና ውስጥ የከተቱ ናቸው።

መንግሥት ለትግራይ ክልል ያለ ምንም ገደብ እርዳታ እንዲደርስ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል ያሉት አቶ ሱራፌል፤ ይህን ተከትሎ አሜሪካ የኢትዮጵያ መንግሥት የወሰደውን ርምጃ አድንቃለች፤ መንግሥትን ላይ ዲፕሎማሲያዊ ጫና ሲያደርሱ የነበሩ ዓለም አቀፍ ተቋማት ጭምር በተለይ የዓለም የምግብ ፕሮግራም በአድናቆት ያዩበትና ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ያላቸውን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ያሻሻሉበት ሁኔታ እንዳለም ጠቁመዋል።



**አቶ ሱራፌል ጌታሁን**

ምዕራባውያን ቀደም ሲል በኢትዮጵያ ላይ የሚያደርጉትን ዲፕሎማሲያዊ ጫና በመተው ድጋፍ ማድረግ መጀመራቸው ዲፕሎማሲያዊ መሻሻሎች መኖራቸውን አመላካች መሆኑን ጠቁመው፤አሜሪካ በኢትዮጵያ በድርቅና በጦርነት ለተጎዱ ዜጎችና አካባቢዎች ድጋፍ ማድረጓ ዲፕሎማሲያዊ መሻሻል እንዳለ አንዱ አመላካች ነው ብለዋል። የዓለም ባንክ ለትግራይ ክልልና በጦርነቱ ለተጎዱ አካባቢዎች መልሶ ግንባታ የሚውል 300 ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ አድርጓል፤ይህም ምዕራባውያን በኢትዮጵያ ላይ የያዙትን የተዛባ የአቋም መተው መለሳለስ ማሳየታቸውን ያመለክታል ብለዋል።

እንደ መምህሩ ገለጻ፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ምዕራባውያን ጫና ከማሳደር ወጥተው በመንግሥት በኩል የተጀመረው የሰላም ጥረት እንደግፋለን እያሉ ነው። ከነበረው ዲፕሎማሲያዊ ጫና በመውጣት ለመንግሥት ድጋፍ ማሳየታቸው የነበረውን የዲፕሎማሲ ጫናና ግፊት መለሳለሱን ማሳያ ነው።

አሁን እየተሻሻለ የመጣው ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ቀጣይነት እንዲኖረው መንግሥት ብዙ ሥራዎች ይጠብቁታል ያሉት አቶ ሱራፌል፤ አሁንም ቢሆን ምዕራባውያን በኢትዮጵያ ላይ ያላቸው አቋም ሙሉ ለሙሉ የተስተካከለ ነው ማለት አንችልም። በኢትዮጵያ ያለውን እውነታ እንዲገነዘቡና የሰላም ሂደቱ ምን ደረጃ ላይ እንዳለና መንግሥት ለሰላም ሲል በሆደ ሰፊነት የሚወስዳቸውን እርምጃዎች ለምዕራባውያን መንግሥታትና ተቋማት የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች ባገኙት አጋጣሚ ማስረዳት አለባቸው ብለዋል።

መንግሥት የሚሠራቸውን የልማት እንቅስቃሴዎች፣የሰላም ግንባታና ብሔራዊ ውይይቶችን በአጠቃላይ የመንግሥትን ቆራጥ ውሳኔ ማስረዳት መቻል አስፈላጊ መሆኑን አመልክተው; ይህ ማድረግ ሲቻል በመንግሥት ላይ የሚደረጉ ዲፕሎማሲያዊ ጫናዎች እንደሚቀንሱ ገልጸዋል።

እንደ አቶ ሱራፌል ማብራሪያ፤ የኢትዮጵያን መንግሥት የሰላም አደናቃፊ፤ በተቃራኒው የሽብር ቡድኑን የሰላም ፈላጊ አድርገው በመሳል የተሳሳተ መንገድ የተከተሉ መንግሥታትን አቋማቸውን እንዲያስተካክሉ ማስረዳት አስፈላጊ ነው።

ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት፣ በጦርነት ጊዜና ከዛ በኋላ የኢትዮጵያ መንግሥት ለሰላም ያለውን ቁርጠኝነት ማስረዳት ከኢትዮጵያ በኩል እንደሚጠበቅ ገልጸው፤ በዲፕሎማሲያዊ መንገድ በማሳመን የምዕራባውያንን ጫና መቀነስ እንደሚቻል አስረድተዋል።

ከምዕራባውያን ድጋፍ ማግኘት የተጀመረውን የሰላም ሂደት ውጤታማ ለማድረግ ያግዛል ያሉት ተመራማሪው፤ ዲፕሎማሲያዊ መሻሻሎች መኖራቸውን ተከትሎ ኢትዮጵያ የአጎዋ ተጠቃሚ እንድትሆን ጠንካራ የዲፖሎማሲ ሥራ መሥራት እንደሚገባ ጠቁመዋል።

# ኢትዮጵያና አንጎላ ግንኙነታቸውን እንደሚጠናከሩ ገለጹ



**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የኢፌዲሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን በኢትዮጵያ ጉብኝት እያደረጉ ከሚገኙት የአንጎላ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቴቴ አንቶኒዮ ጋር በሁለትዮሽ እና ቀጣናዊ ጉዳዮች ዙሪያ ተወያይተዋል።

በውይይታቸውም አቶ ደመቀ ባደረጉት ንግግር÷ ኢትዮጵያ ከአንጎላ ጋር ያላትን ግንኙነት ለማጠናከር እንደምትሠራ ገልጸው÷ በተለይም በኢኮኖሚ ዘርፍ በተለያዩ መስኮች ላይ ተባብሮ መሥራት እና አማራጮችን ማስፋት ይገባል ብለዋል፡፡

"ዓለም በአይገመቴ ሁኔታዎች ውስጥ እያለፈች ነው፤ እንደ አህጉር የከፋ ተፅዕኖ እንዳያሳድርብን በጋራ ተባብረን መሥራት ይገባል" ማለታቸውንም ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ያገኘነው መረጃ ያመላክታል።

አቶ ደመቀ ÷ መንግሥት በሀገሪቱ ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን ለማድረግ የወሰዳቸውን የመተማመኛ እርምጃዎች ለሚኒስትሩ የገለጹ ሲሆን÷ ለአብነትም የተኩስ አቁም ስምምነት፣ያልተገደበ የሰብዓዊ እርዳታ ተደራሽነት፣ ከሰብዓዊ መብት ጥሰት ጋር በተያያዘ እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎችን እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን አብራርተዋል፡፡ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ተቋቁሞ ሥራ መጀመሩንም አስረድተዋል፡፡

መንግሥት በአፍሪካ ኅብረት መሪነት ለሚካሄደው የሰላም ድርድር ቁርጠኛ በመሆን ተደራዳሪ ቡድን ሰይሞ ወደ ሥራ መግባቱን ጠቁመው÷ በማንኛውም ጊዜ የሰላም ድርድሩን ለመጀመር ዝግጁ ነው ብለዋል።

ከሕወሓት ቡድን በኩል ግን የአፍሪካ ኅብረትን ጥረት የማጣጣል እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑንም ነው የገለጹት።

የህዳሴው ግድብ የሦስትዮሽ ድርድርን በተመለከተም÷ ኢትዮጵያ ድርድሩ በመርህ ላይ ተመስርቶ እንዲጠናቀቅ ያላትን ፅኑ አቋም በአጽንኦት ተናግረዋል፡፡

የአንጎላው ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቴቴ አንቶኒዮ በበኩላቸው÷ የኢትዮጵያ መንግሥት ሀገሪቱ ያጋጠማትን ችግር ለማለፍ እየወሰዳቸው ያሉትን እርምጃዎች አድንቀዋል፡፡

"ኢትዮጵያ በነፃነት ትግላችን ወቅት ባለውለታችን ነች" ያሉት ሚኒስትሩ÷ ያን ታሪካዊ ግንኙነት ወደ ኢኮኖሚ ግንኙነት መለወጥ ይገባናል ብለዋል፡፡

በአህጉር አቀፍ ደረጃ ለሚፈፀሙ የኢኮኖሚ ስትራቴጂዎች ተፈጻሚነትም በጋራ መንቀሳቀስ እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

## ለግብርና ዘርፉ በተሰጠው ትኩረት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የእርሻ መሬትም በዘመናዊ የግብርና ማረሻ መሳሪያዎች (ትራክተር) መታረሱ የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ መረጃ እንደሚያመለክት አስረድተዋል፡፡

እንደ ዶክተር ፍጹም ገለጻ፤ በአሁኑ ወቅት ከስድስት ሺ በላይ ትራክተሮች አሉ፡፡ ካለፉት አራት ዓመታት በፊት የነበሩትን ጊዜያቶች መለስ ተብሎ ሲቃኝ በግብርናው ዘርፍ ከግብዓት አቅርቦት ጀምሮ ለውጡ ከፍተኛ ነው፡፡

በተጨማሪም ለመስኖ ልማት የሚውሉ የውሃ ስበት መጠቀሚያ(ፓምፕ)ግብዓቶችም እንዲሁ ለግብርናው እንዲያግዙ እየተደረገ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡ ለነዚህ ግብዓት ኢንቨስት ማድረግ (መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ) ትላልቅ የመስኖ ግድብ መሥራት ሳያስፈልግ ከወንዞች ውሃ በመጥለፍ ሰፊ ልማት በማከናወን የሰዎችን ኑሮ መቀየር ያስችላል ብለዋል፡፡

በአሁኑ ጊዜም በፀሐይ ብርሃን አገልግሎት የሚሰጡ ከ20ሺ ያላነሱ ፓምፖች ጥቅም ላይ እየዋሉ መሆናቸውን ያስረዱት ዶክተር ፍጹም፤ ግብዓቱ በተፈጥሮ ኃይል ጥቅም እንዲሰጥ በማድረግ የኤሌክትሪክ ኃይልን መቆጠብ መቻሉንም ገልጸዋል፡፡ መሬትን የኢኮኖሚ መሣሪያ ለማድረግ መንግሥት ባደረገው እንቅስቃሴም አርሶ አደሩ የመሬት ሰርተፊኬት (ምስክር ወረቀት) እንዲኖረውና በምስክር ወረቀቱ እንዲገለገል እንዳስቻለው አስረድተዋል፡፡

በተለይም አርሶአደሩ የምስክር ወረቀቱን አስይዞ ከባንክ እንዲበደር ዕድል መፈጠሩንና የክላስተር (ኩታገጠም የአስተራረስ ዘዴን በመከተል የግብርና ሥራው እየተከናወነ መሆኑን እንዲሁም፤ እስካለፈው ሳምንት ድረስ ባለው መረጃ የኦሮሚያ ክልል 75 በመቶ በኩታገጠም የአስተራረስ ዘዴ መጠቀም መቻሉንም ሚኒስትሯ አመልክተዋል፡፡

እንዲህ ያለው እንቅስቃሴ ለምርትና ምርታማነት እድገት ትልቅ የሚባል ለውጥ እንደሆነ የገለጹት ዶክተር ፍጹም፤ የኢኮኖሚያዊ መዋቅራዊ ሽግግር ለማሳካት በመካከል ላይ የሚሠሩ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ መኖራቸውንም ጠቅሰዋል ፡፡ በየዓመቱ የሚከናወኑ ተግባራት በረጅም ጊዜ ለተያዘው ዕቅድ መሠረት መሆናቸውንም ገልጸዋል፡፡

## ከ69 ሚሊዮን ዶላር በላይ ወጪ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እየተከናወኑ መሆኑን የገለፁት ኃላፊዋ፤ ደረቅ ወደቡ አሁን ላይ መገንባቱ ከበርካታ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጥቅሞቹ ባሻገር መንግሥት ላሰበው ለነፃ የንግድ ቀጠና እንደሚጠቅም አንስተዋል፡፡

እንደ ወይዘሮ እመቤት ገለፃ፤ የድሬዳዋ ደረቅ ወደብና ተርሚናል የገቢና የወጪ የንግድ እንቅስቃሴውን የተቀላጠፈ በማድረግ፤ ለዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር እና ለወደብ ኪራይ የሚወጣውን ወጪ በማስቀረት ከፍተኛ ፋይዳ ይኖረዋል ብለዋል፡፡

በቻይናው ሲቪል ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን እየተከናወነ የሚገኘው የግንባታ ፕሮጀክቱ ከድሬዳዋ መስተዳድር በተገኘ 34 ነጥብ 1 ሄክታር መሬት ላይ ያረፈ ነው፡፡ የፕሮጀክቱ በኢትዮጵያ ባሕር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ድርጅት ባለቤትነት እየተገነባ ሲሆን በአጠቃላይ 69 ሚሊዮን 589 ሺህ 56 ዶላር ወጪ ጠይቋል፡፡

የደረቅ ወደቡ ግንባታ ሲጠናቀቅ በተለይም የገቢና ወጪ ንግድን ለማሳለጥ ከማገዙም በላይ በጅቡቲ ወደብ ላይ ለብዙ ጊዜ በክፍያ ይቀመጡ የነበሩ ኮንቴይነሮች ወደ ደረቅ ወደቡ ተጓጉዘው እንዲከማቹ በማድረግ ሀገሪቱ የምታወጣውን የውጪ ምንዛሪ እንደሚቀንስ ታምኖበታል፡፡

ደረቅ ወደቡ ደረጃውን የጠበቀ የተሽከርካሪዎችና ኮንቴይነሮች ጋራዥ እንዲሁም በባቡር የሚገቡ ኮንቴይነሮች የክብደት ሚዛን አገልግሎት የሚሰጥ



ወይዘሮ እመቤት ፍሰሐ

ይሆናል፡፡

በሀገሪቱ የሚገኙ ደረቅ ወደቦችን በማስፋት በተለይ በሎጅስቲክሱ ዘርፍ ኢትዮጵያ ለአፍሪካ መግቢያ በር ሆና እንድታገለግል ለማድረግ እየተሠራ እንደሆነ የትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ መግለፁ የሚታወስ ነው፡፡

ሚኒስቴሩ ከደረቅ ወደብና ተያያዥ የሎጅስቲክስ ወጪዎች ከ2 ቢሊዮን ብር በላይ ማዳን መቻሉንም በ11 ወር ሪፖርቱ ጠቅሷል፡፡

ኢትዮጵያ ወደብ አልባ ሀገርነቷ የሚያስከትልባትን ተፅዕኖ ለመቀነስ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ደረቅ ወደቦችን ገንብቶ ወደ አፍሪካ የሚጓጓዙ ጭነቶች እንዲጓጓዙባት በማድረግ ለአፍሪካ መግቢያ በር ሆና እንድታገለግል እየተሠራ እንደሆነ አክሎ መጥቀሱም የሚዘነጋ አይደለም፡፡

## የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ያለባቸውን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንትና የፌደራል ፍርድ ቤቶች ቃል አቀባይ አቶ ተስፋዬ ንዋይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ያለባቸውን የመዝገብ ጫና ለማቃለል መደበኛ ሥራቸውን ለአንድ ወር እንዲቀጥሉ ተወስኗል።

ወደ 2015 ዓ.ም የሚያልፉ መዝገቦችን ቁጥር ለመቀነስ፣ የበሰሉ መዝገቦችን እልባት ለመስጠት፣ እስረኛ ያለባቸውን መዝገቦች ቅድሚያ ሰጥቶ ለመሥራት እንዲያስችል የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ከነሐሴ አንድ ቀን እስከ ነሐሴ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ መደበኛ የዳኝነት አገልግሎት ይሰጣሉ።

ዳኞች ዓመቱን ሙሉ እጅግ አድካሚ የሆነ የዳኝነት አገልግሎት ሲሰጡ ቆይተዋል ያሉት አቶ ተስፋዬ፤ በሂደቱም አወንታዊ ውጤቶች ተገኝተዋል ብለዋል። ተግባሩ ሥራውን በበለጠ ውጤት ለማስቀጠል እንደሚያስችልና በዳኞች ፍቃደኝነት ላይ በመመሥረት የተሰጠ ውሳኔ መሆኑንም ተናግረዋል።

በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/13 አንቀጽ 38 (2) መሠረት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ከነሐሴ 1 ቀን ጀምሮ እስከ መስከረም 30 ባለው ጊዜ ዝግ እንደሚሆኑ የሚደነግግ መሆኑን፣ በዚህ ጊዜ ውስጥ ዳኞች ባላቸው የትርፍ ጊዜ አስቸኳይ የሆኑ ጉዳዮችን ብቻ ሊያስተናግዱ እንደሚገባ አዋጁ ማስቀመጡንም አስታውሰዋል።

የፌዴራል ፍርድ ቤት ዳኞች ያላቸውን የእረፍት ጊዜ መስዋዕት በማድረግ መደበኛ የዳኝነት አገልግሎት ለመስጠት ፍቃደኛ በመሆናቸው ፍርድ ቤቱ ያመሰግናል፣ ተገልጋዩም በዚሁ አግባብ አገልግሎት ለማግኘት ተገቢውን ሊያደርግ ይገባል ብለዋል።

የፌደራል ፍርድ ቤቶች በ2014 ዓ.ም በሕገ መንግስቱና በሕግ የተጣለባቸውን የዳኝነት አገልግሎቶች ሲሰጡ መቆየታቸውን ጠቁመው፤ በ12 ወራቱ 209 ሺህ 317 መዛግብት በሶስቱም የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ቀርበው 176 ሺህ 797 ለሚሆኑ ጉዳዮች እልባት መስጠት መቻሉንም ገልጸዋል።

ከሰኔ 2014 ዓ.ም ወደ ሐምሌ 2014 ዓ.ም የተላለፉ መዛግብት 32 ሺህ 520 ሆነው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች እየታዩ እንደሚገኙም አመልክተዋል።

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አማካኝነት የማጥራት አቅም 103 ነጥብ ሰባት፣ የመጨናነቅ ሁኔታ አንድ ነጥብ 18 እንዲሁም የክምችት ምጣኔ ዜሮ ነጥብ 18 ሲሆን በበጀት ዓመቱ ወደ 300 የሚሆኑ መዝገቦች በፍርድ ቤት መር አስማሚነት ሥርዓት እልባት እንዲያገኙ መደረጉንም ነው የጠቆሙት።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት አፈጻጸም የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍትሐ ብሔር ጉዳዩች ፍሰት አስተዳደር መመሪያን መነሻ በማድረግ ጉዳዮች እንደየተናጠል ባህሪያቸው እና የጊዜ ገደባቸው እልባት እንዲሰጣቸው ሲደረግ ቆይቷል። በዚህም በሶስቱም ፍርድ ቤቶች በአማካይ 90 በመቶ የሆኑ ጉዳዮች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ እልባት እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል።

የወንጀል ጉዳዮችን በተመለከተ እስረኛ ያለባቸው መዛግብት ቅድሚያ ተሰጥቶ እልባት እንዲሰጣቸው በማድረግ እየተሠራ ይገኛል። የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የ2014 ዓ.ም የ12 ወራት የእቅድ አፈጻጸም ከዓለም አቀፍ የፍርድ ቤቶች ውጤታማነት መለኪያ መስፈርቶች አንጻር ሲታይ የውጤታማነት ደረጃው ከፍተኛ መሆኑን ያመለክታል ብለዋል። ዝርዝር የፍርድ ቤቱ ዓመታዊ ሪፖርት በቅርቡ ይፋ እንደሚሆንም ለማወቅ ተችሏል።

## ‹‹የትግራይ ሕዝብ የሕወሓት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በየጣቢያው እና በየወረዳው ቅስቀሳ በማድረግና በማስገደድ ላይ ናቸው ብለዋል።

ጦርነት ለትግራይ ሕዝብ አይጠቅምም፤ ሕዝቡም የሚፈልገው ሰላም ነው፤ ከዚህ በፊትም በተደጋጋሚ በተደረጉ ጦርነቶች የትግራይ ሕዝብ ልጆቹን ከመገበር ኣልፎ የተጠቀመው ነገር የለም ሲሉ አስረድተዋል።

የትግራይ ሕዝብ ከሁሉም በፊት ሰላም ፈላጊ ነው ያሉት፤ ኮሎኔሉ፤ ሕወሓት ከሕዝብ ፍላጎት ውጪ ‹‹ሶስተኛ ዘመቻ›› እያለ እያደረገው ያለው የጦርነት ቅስቃሳ ተጨማሪ ውድመት የሚያስከትል በመሆኑ የትግራይ ሕዝብ በፅኑ ሊያወግዘው ይገባል ሲሉ አሳስበዋል፡፡

የትግራይ ሕዝብ ችግር ሊፈታ የሚቻለው ሰላም ሲኖር እንጂ ሕወሓት እየተከተለው ባለው መንገድ ስላልሆነ የትግራይ ሕዝብ ያለፉት ጦርነቶች ይበቃል በማለት በሕወሓት ላይ ጫና እንዲያደርግ ጥሪ አቅርበዋል።

ሰላም ከተፈጠረ የወደሙ መሠረተ ልማቶችን ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ በጋራ ተባብሮ ሊገነባው ይችላሉ ያሉት ኮሎኔል ፍስሐ፤ ተመልሶ ወደ ጦርነት ከተገባ ግን የቀሩት ጥቂት መሠረተ ልማቶች ሙሉ በሙሉ ሊወድሙ እንደሚችሉ ተናግረዋል።

የሕወሓት ቡድን ወደ ሰላም እንዲመጣ የሃይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎችና ታዋቂ ሰዎች ጫና ማድረግ አለባቸው ሲሉም አሳስበዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የመንግሥትን ገንዘብ ያለአግባብ በሚያባክኑ አካላት ላይ አስተማሪ ርምጃ ሊወሰድ ይገባል!

የመንግሥት በጀት ውስን ነው። ይሄ ውስን ሀብት የሚሰበሰበው ከእያንዳንዱ እናት መቀነት ተፈትቶ ከታክስና ግብር ነው። በመሆኑም በአግባቡ ሕግና ሥርዓትን ተከትሎ ለሀገር ልማትና ዕድገት መዋል እንዳለበት ይታመናል። በየመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የሚመደበውን በጀትም በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋል ይገባል።

የመንግሥት ግዢዎች ፣ ለግንባታ የሚወጣ ወጪ፣ ትላልቅና ትናንሽ ፕሮጀክቶች ግንባታ በሚካሄድበት ጊዜ ፣ ወጪና ጉልበት ቀናሽ በሆነ መልኩ ጥራታቸውን የጠበቁ መሆን አለባቸው። ሁሉም የሀገር ሀብት የሁሉም ዜጋ ሀብትና ንብረት ነውና ይሄንኑ ውስን ሀብት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋል ከሁሉም ዜጋ የሚጠበቅ ይሆናል።

ይሁን እንጂ አሁን ባለው ሁኔታ የመንግሥት ሀብትና ንብረት አለአግባብ ሲባክን ይታያል። በእውቀት ማነስ ፣ በቸልተኝነት፣ ወይም ደግሞ ወደ ግለሰቦች ኪስ እንዲገባ ታስቦና ታቅዶ የገንዘብ ብክነት ሲፈጸም ይስተዋላል። ይህን የሚመለከት ሠራተኛ፣ ተቆጣጣሪ እና ኃላፊ ብልሹ የሆነ አሠራር ሲኖር ሕግና ሥርዓት እንዲይዝ ማድረግ ፤ ከዚህም አለፍ ብሎ እርምጃ እንዲወሰድ ጭምር መሥራት አለበት ። ነገር ግን አሁን በሚታየው ሁኔታ የሚባክነው የመንግሥት ሀብት እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ እንዳልሆነ ከፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት የሚገኙ መረጃዎች ያመላክታሉ።

የዚህም ዋና ምክንያት ተደርጎ የሚጠቀሰው የመንግሥት መሥሪያ ቤት አሠራርን ያለማወቅና ከብቃት እንዲሁም ክህሎት ማነስ ጋር ተያይዞ ነው። የመንግሥት የአሠራር ሥርዓትን ባለመከተል፣ በቸልተኝነት እና በድፍረት እየተፈጸመ ያለ የአሠራርና የሕግ ጥሰቶች በመኖራቸው ምክንያት ነው ።

በመሆኑም ለተቋማት የሚመደብ በጀት ፤ ለፕሮጀክቶች የሚመደብ ገንዘብ በአግባቡና በወቅቱ ለታለመለት ዓላማ እንዲውል ማድረግ ይገባል። ለዚህም የቅርብ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ በአጥፊዎች ላይም አስተማሪ ቅጣት መውሰድ ያስፈልጋል። ብልሹ አሠራርን በማጋለጡ ሂደት በተለይ ደግሞ የውስጥ እና የውጪ ኦዲተሮች ትልቅ ኃላፊነትና የሕዝብ አደራ አለባቸው። የእያንዳንዱን ተቋም የፋይናንስ ሥርዓት በመመርመር ሪፖርት ማድረግ፣ ብልሹ የሆኑ አሠራሮችንም ማጋለጥና ለነገ ትምህርት እንዲወሰድባቸው ማድረግ ይገባቸዋል ።

ከዋና ኦዲተር ባገኘነው መረጃ መሠረት፤ አሁን ባለው ሁኔታ የመንግሥት ተቋማት ያለአግባብ ወጪ ሂሳብ ግኝቶች እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ አይደለም። የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የሚመዘገብ ሒሳብ፣ ደንብና መመሪያን ሳይከተሉ ግዥዎች መፈጸም ፣ ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ የማይቻል የወጪ ሂሳብ ግድፈቶች የመሳሰሉት ተጠቃሽ ናቸው።

ከ2008 እስከ 2013 ዓ.ም ድረስ ያለውን በንጽጽር ሲታይ በ2008 ዓ.ም ያለአግባብ የወጣው ወጪ 826 ነጥብ 4 ሚሊዮን ብር ሲሆን ከስድስት ዓመት በኋላ አሁን ይሄ ቁጥር ወደ አራት ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ብር አሻቅቧል ፡፡ ይሄ ሲታይ ያለአግባብ የሚወጣው ወጪ እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ አለመሆኑን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል ። ይህም የመንግሥት ሀብት በአግባቡ ለታለመለት ዓላማ እንዳልዋለ የሚያመላክት ነው። በመሆኑም ተቋማትን የሚመሩ አካላት በየጊዜው በኦዲቱ የሚሰጣቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች መነሻ በማድረግ እርምጃዎችን ከስር ከስር መውሰድ አለባቸው።

አሁን እየታየ ያለው ከጊዜ ወደ ጊዜ ከመስተካከል ይልቅ የሕግ ጥሰቶች፣ የግዥ ሥርዓቱን ተከትሎ ያለመሄድ ሁኔታ እየጨመረ ነው። በመሆኑም የዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት በየተቋማት ያሉትን ችግሮች በመለየትና የሂሳብ ግኝቶችን ወደ አደባባይ በማውጣት ጥሩ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል። የፋይናንስ ሕግና ሥርዓትን ተከትለው የማይሠሩ ወይም ያልሠሩ ተቋማትን የኦዲት ሪፖርት ለፓርላማው ከነስማቸውና ጉድለታቸው በማቅረብ በአደባባይ ማጋለጥ ጀምሯል። ይሄ ይበል የሚያሰኝ ጅምር ነው ። ሆኖም ግን በቂ ነው ማለት አይደለም።

አሁንም ቀጣይ ሥራዎች መኖር አለባቸው። ከኦዲት ግኝት ሪፖርቱ በመነሳት ጉዳዩ የሚመለከተው አካልም መውሰድ የሚገባውን ሕጋዊ እርምጃ መውሰድ አለበት። በሕግ አግባብ መጠየቅ ያለበት አካል ካለም ሳይሸፋፈንና የስልጣን ደረጃው ሳይለይ በሕግ አግባብ ተጠያቂ መደረግ አለበት። ይሄም ልክ እንደ ኦዲት ሪፖርቱም ውጤቱ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲሁም ለሕዝቡ መግለጽ ያስፈልጋል።

መወሰድ በሚገባው ልክ እርምጃ ካልተወሰደም የኦዲት ግኝት መኖሩን ያሳወቀው ዋና ኦዲተር የሥራውን ውጤት ቢያቀርብም እርምጃ መውሰድ የሚገባው አካል ግን ኃላፊነቱን አልተወጣም ሲል የተቋማቱን ስም በግልጽ ለፓርላማው ማሳወቅ ይኖርበታል። የዚህ ጉዳይ አስፈላጊነት አንዱ ከሌላው እንዲማር ለማድረግ ነው። ስለዚህ በቀጣይ ዋናው ኦዲተር አሁን ካደረገው እርምጃ አለፍ ብሎም በዚህ ልክ ሥራቸውን ያልሠሩና ኃላፊነታቸውን ያልተወጡ ተቋማትና የሥራ ኃላፊዎችን ማጋለጥ ይገባዋል። የመንግሥትና የሕዝብ ገንዘብና ሀብት ለታለመለት ዓላማ እንዳይውል ያደረጉና ለግል ጥቅማቸው ያዋሉትንም ማጋለጡን አጠናክሮ መቀጠል አለበት! የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትም ግኝቶቹን ተከትሎ አስተማሪ እርምጃ መውሰድና ማስተካከል ለነገ ይደር የማይባል ሥራ ሊሆን ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የሰላም መንገዳችን ቅድመ ሁኔታ የሕዝብ ጥቅም ይሁን

ብስለት

የእናትነት መስፍሪያ ልኩ ዓለም ላይ ያልተፈጠረ ይመስል ቃል ያጣል። እናትነት ደመነፍሳዊ ነው። እንዲህ ላድርግ፤ እንዲህ ልሁን ብለህ የምታደርገው ሳይሆን፤ ዝም ብሎ ከሴትነት ጋር ከመውለድ ጋር አብሮ የተሰጠ የተፈጥሮ ፀጋ ነው። እናት ስትሆን ልጆችህ በልተው መጥገባቸውን ማመን የማትችል፤ ወድቀው መነሳታቸው ተአምር የሚሆንብህ፤ የነገ ስኬታቸውን ስዕል በዓይነ ህሊናህ ስለህ ለዛ መሳካት ሌት ከቀን የምትደክምበት ጉዞ ነው።

ታዲያ ይሄን በተስፋና በፍቅር ያለድካም የሚደረግ ጉዞ፣ ሰዎች ነንና በተለያየ መንገድ ሲደናቀፍ ይታያል። ልጆች የፈለጉትን ጠይቀው አለማድረግ ህመም የሚፈጥርባት እናት፣ በጦርነት ምክንያት ቤቷ ተዘግቶ የልጆቿን የረሃብ ሲቃ እንድታዳመጥ የምትገደድበት ገጠመኝ ይፈጠራል። ነጋቸውን በአእምሮዋ ስላ ለስኬቱ የምትተጋው እናት፣ ልጆቿ ከትምህርት ገበታ ከተለያዩ ቀናት ብሎም ወሯት ከዛም ዓመታትን ስታስቆጥር ምን ያህል ሊያሳቅቃት እንደምትችል በእሷ ቦታ ሆኖ ማሰቡም ቀላል አይደለም።

መኖር ጥያቄ ውስጥ ገብቶ ልጆቿን መልሳ አትውጣቸው ነገር ግራ ገብቷት መደበቂያ መሸሸጊያ ጥጋት ያጣችውን እናት እንባ ማየት፤ እሷም ሰው ናትና ጠኔ እያዳፋት ከአፏ ነጥላ ልጆቿን ልታቃምስ የምትጥርን እናት፤ የእምነቷ ጥልቀት ተፈትኖ የፀሎቷ ምላሽ መምጫ እንደ ምፅአት ቀን ለራቀባት እናት፤ ጭንቀትና ስቃይዋን ቦታ ላልሰጠኸው ለአንተ በሁለት ጎራ ቆመህ ቅድመ ሁኔታ እያልክ የሰላምን ቀን ለምታረዝመው ምን ትርጉም ይሰጥህ ይሆን?

ረሃብ ስንት ቀን እንደሚፈጅ ላልገባህ ለአንተ፤ ማጣት ትርጉሞ በእሷ እጦት ልክ ላልተገለፀልህ ለአንተ፤ መንገዱን ጀምረህ እንቅፋት ለምታኖረው ለአንተ፣ በሷ ጫማ ውስጥ ብትሆን ሕመሙ ምን ያህል ሊሰማህ ይሆን? ብዬ ልጠይቅህ ወደድኩ።

የአንድ እናት ልጆች፤ መጠሪያ ቋንቋቸው አንድ የሆነ፤ ቀለም ዘራቸው ያልተለየ፤ በአንድ ማህፀን ግፊያን ያቆሙ ዘንድ ለሰላም ንግግር ለመቀመጥ ይሁንታቸውን ሰጥተዋል የሚለውን ዜና ስሰማ እፎይ ብያለሁ። መሪዎቻችንም ሰላም ቋንቋችን ሊሆን ስለሰላም በጋራ ተነጋግረን ለመግባባት ፈቅደናል ብለውናል፤ ይህ ይበል የሚያሰኝ ውሳኔና ተግባር ነው።

ለሕዝብ ለወገናችን ስንል፤ ያሉት ነገሮች እስከሚስተካከሉበት ጥግ ድረስ ጥረታችንን አናቆምም ሲሉንም፤ እኛም «አቦ ያድርገው፣ እንዳፋችሁ ይሁንልን» ብለናል። ለመስማማት ማሰባችሁ እንደው የነገዋን ጀንበር ሳያያት በአጭሩ የሚቀጨውን ወገን ካስቀረልን፤ የሰቆቃ ድምፆችን ከየአቅጣጫው መስማት ከቀነሰልን ከፈጣሪ የተማከራችሁ ለሰላም ቅድሚያ የሰጣችሁ ዕድሜያችሁን ያርዝመው ስንል መርቀናል።

እርቁም የሚነገር ብቻ ሳይሆን የሚተገበር ይሆንልን ዘንድ ምኞታችን ነው። እንደውም ሰሞኑን በመዲናችን አዲስ አበባ አትሌቶቻችንን የጀግና አቀባበል ስናደርግላቸው ገሚሱ እንባ እንባ እያለው እልልታውን ሲያቀልጥ፤ ገሚሱ ምነው ይሄ ድል ጥላቻን አፈር ከድሜ አስግጦን በአንድነት ወደፊት የምንጓዝበት መንገድ መጥረጊያ ቢሆንልን እያለ ሲመኝ ነበር።

ከእግር እስከ እራስ በሚወር ኢትዮጵያዊ ስሜት፣ ድላቸው እንጂ ብሔራቸው ያልተጠየቀበት፤ አገርን ማስቀደማቸው እንጂ መምጫቸው ከየት ነው? እንዴት ነው ባልተባለበት ልክ ሙሉ የደስታ መንፈስ ፊታቸው ላይ እየታየ አስደስተው እንዳስለቀሱን ጀግኖች አትሌቶቻችን ፖለቲከኞቻችንም ጀግንነት ገድሎ መሞት እንዳልሆነ ተማሩልን እንላለን።

ምክንያቱም፣ ጀግንነት ከጦርነት የላቀ መፍትሄን አሻግሮ በመመልከት አንድ እርምጃ ወደ ፊት ማራመድ ሲችል፤ ጀግንነት ጦር ሜዳ ሳይዋል በፍቅር ገድሎ በዓለም መድረክ ላይ ቀና ሲያስብል፤ ወታደር አገር እንጂ ብሔር የለውም አገር ደግሞ ኢትዮጵያ ናት የኢትዮጵያ ልጆች ደግሞ በእኩልነት በአንድነት ይኖሩ ዘንድ ጀግና አሻጋሪዎች ያሿታልና መውጫ መግቢያው ተዘግቶባት ማጣፊያው ላጠራት እናት እስኪ ለሰላም የሚተጋ ጀግና ሆናችሁ አሳዩን።

ጥርጣሬን ከውስጣችሁ አውጥታችሁ አንድ ጠረጴዛ ላይ ለመቀመጥ እርስ በእርሳችሁ ተማመኑ። እምነት መስመማትን፤ መስማት ደግሞ መግባባትን፣ መግባባትም ሰላምን፣ ሰላም ደግሞ እርቅን ያመጣልና በቅድሚያ ወንድማማችነታችንን በማመን ልዩነቶቻችን የሚታረቁበት መንገድ ላይ ትኩረት ይደረግ።

ለዚህ ደግሞ ለሰላም ዓይኔን አላሸም ካላችሁ፤ ቅድሚያ መስፈርት መሆን የሚገባው የሕዝብ ጥቅም ነውና ልጆቹን ምን ላብላ ምን ላልብስ ያለችውን እናት አስባችሁ ልባችሁ ላይ የከበደውን ነገር ቀለል አድርጉት። ምክንያቱም የሰላሙ ጥረት አንድ ቀን በረዘመ ቁጥር እየጠፋ ያለውን ነፍስ እያሰባችሁ የማይታረቅ ነገር ውስጥ ከመግባታችን በፊት ፈጠን ያለ ጥረት በትህትና ለማድረግ ልባችሁን አዘጋጁ።

መቼስ እግርና እግርም ይጋጫል፤ እናም ሰው ለሰው ቢጋጭ ለምን ተጠላን የሚያስብል ነገር የለም። ፀባችንን በምን እንፍታው? ምን ብለን ምን አድርገን አገር ሰላም እንዲሆን ሕዝባችን በአማን እንዲያደር ልናደርገው እንችላለን? ከሁሉ በላይ ያለጥፋቱ ዋጋ የሚከፈለው ሕዝብ ባላየው ባልገባው ነገር ለሚማገደው ወጣት ነገ አገር ተረክበው አገሩን ከታላላቆቹ አገራት ተርታ ለሚያሰልፉት ሕፃን ስንል ሰከን ማለት ተገቢ ነው።

መቼስ ሰው ከላይ ሲሆን ራሱን ለማሳወቅ የተዘጋጀ ነው የሚል እምነት አለን። ከበላይ ያለው ግን ወደ ላይ ብቻ ማንጋጠጥ ሳይሆን ወደ ታቹም ወደ በታቹም በመመልከት የወገኑ ቁስል አካሚ፤ የተከፋችትን እናት እንባ አባሽ ሊሆን የተገባ ነው። ይሄን ማድረግ ካልቻለማ ምኑን ከላይ ሆነ?

ይሄንን ያህል «የቀበጣጠረኩት» መቼም ከእናንተ አውቄ ሳይሆን፤ ከትንሽየዋ የግንዛቤ ጓዳዬ ትዝ ያለኝን ሃሳብ ላስታውሳችሁ ብዬ ነው። ምክንያቱም እንደ ብዙዎቹ እንና እኔን መሰሎች ከፍቶናል፤ ማታ ተኝተን ነገ ስለሚሆነው ነገር በተስፋ መጠበቅ ቀርቶ የፈጣሪን ቸርነት እያመሰገንን ተስፋ በማጣት ውስጥ መንከላወስ ደክሞናል። ሞት በዝቶ እኛን ማስደንገጥ ካቆመ ሰነባብቷል፤ ችግር ሲበዛ አደንዝዞን ይሆን ሌላ ዝም ብሎ የእውር ድንብር መነዳት ሆኗል፤ እና ከዚህ መደናዘዝ ከዚህ ተስፋ ማጣት ውስጥ ታወጡን ዘንድ እንማፀናለን።

የረሀብን ልክ ዙሪያው ገባው እንደተዘጋባት እናት ያህልም ባይሆን አንድ ቀን ቢጎል የሚሰማንን አስበን ለሰላም ዝቅ እንበል። ከሰላሙ መንገድ በኋላ ተከታይ ጥያቄዎች ቢኖሯችሁ በሰላሙ ሜዳ ለመወያየት ቀነ ቀጠሮ ይዛችሁ በየቀኑ ለሚረገፈው ወገን ስትሉ አንድ እርምጃ ወደ ሰላም በመራመድ ጀግንነታችሁን አሳዩን።

ለእኔ ጀግና ለተከፋ ወገኑ ደራሽ፤ በኀዘን ለተቆራመደው እንባ አባሽ ነው። ለእኔ ጀግና እልህ ድንፋታውን ትቶ ስለ ሰላም ቆርጦ የሚራመድ ነው፤ ለእኔ ጀግና ዘር ቀለም ጎጥ ሳይለይ ሁሉን በአንድ የሚያይ፣ የሕዝብን የመከፋትና ተስፋ የማጣትን ባህር እንደሙሴ በበትሩ ለሁለት ከፍሎ ወደ ሰላም ደሴት የሚያሻግር ነው።

መሪም በመሪነቱ ልክ፤ ሕዝብም እንደሕዝብ ሆኖ አዲሱን ተስፋ በሰላም የምንቀበል፤ የእናት መሶብ ሞልቶ ለልጆቹ ምን ልስጥ ምን ልቁረስ ተረት የሚሆንበት፤ ወገን እንደቅጠል መርገፉ ቀርቶ ለልምላሜ ለተስፋ በመሥራት ወደ ከፍታው የምንሻገርበት ዘመን እንዲያመጣልን እየተመኘሁ የዛሬውን አበቃሁ። ለዚህ ደግሞ የሰላም መንገድ ጉዟችን ቅድመ ሁኔታችን የሕዝብ ጥቅም ይሁን፤ ይሄ ሲሆን ሰላም ከፍታዋን፤ ድንፋታም ውድቀቷን ይጎናጸፋሉ።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

## እርቅ - ደም ያድርቅ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ያኔ ድሮ ድሮ..፣ እንደ አሁኑ በዘርና በጎሳ ሳንከፋፈል በፊት፤ ሀገራችን በእኛ እኛም በሀገራችን ነበር የምንታወቀው። ያኔ ድሮ..እንደ አሁኑ በብሄርና በሀይማኖት ከመለያየታችን በፊት አንድ ህዝቦች፣ አንድ አብራኮች ነበርን። አሁን ሁሉም ነገር ሌላ ነው። አንድነት ያቆነጀው ኢትዮጵያዊ መልካችን ዘርና ጎሳ፣ ብሄርና ሀይማኖት ገብቶበት ወይቧል። ስማችን ጠፍቶብናል። ማናችሁ ስንባል ኢትዮጵያዊ ነን ብለን በኩራት እንዳልተናገርን፤ ዛሬ ማናችሁ ላለን የምንናገረው ብዙ ጥላቻ ወለድ ስሞችን አትርፈናል። በአንድ ያቆሙን ኢትዮጵያዊ ስሞቻችን ዛሬ ላይ ከምንም በላይ የሚያስፈልጉን የሰላማችን ቀንዲሎች ናቸው። የወየብነው እውነትን ሰውረን በሀሰት ስላጌጥን ነው። ከኢትዮጵያዊነት በፊት ያሉ ስሞች ሁሉ የሀሰት ስሞች ናቸው። ያደመቀን፣ ሶስት ሺ ዘመናትን በታሪክና በስልጣኔ ያሻገረን ኢትዮጵያዊነት ነው። ኢትዮጵያ የሚለው ስም። ይሄ ስም መቅደም አለበት።

ድሮ ኢትዮጵያዊ ብቻ ነበርን፣ ድሮ ሀገር ብቻ ነበርን። አሁን ብዙ ነን። አንዷን ሀገራችንን ከፋፍለን አማራና ኦሮሞ፣ ትግሬና ጉራጌ አድርገናታል። ድሮ ሰው ነበርን፣ ድሮ አለም ያደነቀን የእውነትና የፍትህ ሚዛኖች ነበርን፤ አሁን ሌላ ነን። ወንዝ የማያሻግሩንን ፖለቲካ ወለድ ስሞችን ተነቅሰን ለጠየቀን ሁሉ እኔ አማራ ነኝ፣ እኔ ኦሮሞ ነኝ፣ እኔ ትግሬ ነኝ ስንል በአንድነታችን ውስጥ መርዝ እንረጫለን። ድሮ ሩህሩህ ነበርን፣ አይደለም እርስ በርስ ልንገዳደል ቀርቶ የተማረኩ የጠላት ምርኮኞችን አብልተንና አጠጥተን ተንከባክበን የምንሸኝ የአምላክ ባሮች ነበርን። ዛሬ ሌላ ነን። መግደል የሚያረካን፣ ማሰቃየት የሚያስደስተን የሳጥናኤል ጭፍሮች ወጥቶናል። በጋራ ብንኖርባት የምትበቃንን፣ በፍቅር ብንኖርባት የምትሰፋንን አንዷን ኢትዮጵያ ብዙ ቦታ ከፋፍለን እንዳትበቃን እንፈራገጥባታለን። እንገፋፋባታለን። ተንፈራግጠን..ተንፈራግጠን እኛ ወድቀን ሌሎችንም እንጥላለን። ተጋፍተን ተጋፍተን ማንም የማይኖርባትን ሀገር እንፈጥራለን። ትርፋችን ይሄ እኮ ነው። የመንፈራገጥ..የመጋፋት ትርፉ ተያይዞ መውደቅ ነው። ተያይዞ መቆም እያለ፣ ተቃቅፎ መኖር እያለ ለመውደቅ መገፋፋት ምን የሚሉት ብሂል እንደሆነ አልገባኝም።

መንፈራገጥ አንድም ለመውደቅ አንድም ለመላላጥ ነው። ብሄሩን ትልቅ አድርጎ ሀገሩን ያሳነሰ፣ ዘሩን ኩሩ አድርጎ ሰውነቱን ያኮሰሰ የኋላ ኋላ ከመውደቅ የሚያግደው አይኖርም። አለም ላይ ከሀገራቸው ብሄራቸውን ያስቀደሙ፣ ከሰውነታቸው ዘራቸውን ያስቀደሙ ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች የወደቁ ናቸው። ውሻ በጨው የማይቀምሳቸው የታሪክ ነውረኛ ናቸው። የእኛም በብሄር ስም መንፈራገጥ አንድም ለመውደቅ አንድም ለመላላጥ አንድም ነውረኛ ታሪክ ለመጻፍ ነው። ለሁላችን የምትበቃ ሀገር አለችን፣ በጋራ እሴት፣ በጋራ ባህል የተሳሰረ ማንነት አለን በዚህ እውነት ውስጥ ጸንቶ መኖር እንጂ ለመውደቅ መገፋፋት ትርፍ የለውም። ኢትዮጵያ ሀገራችን አንድ ናት..በአንድ ሀሳብ፣ በአንድ ህልም ያጸናናት የጋራ ቤታችን ናት። የአባቶቻችን አንድነት ምሰሶ ሆኖ፣ ዋልታና ማገር ሆኖ ያቆማት ናት። እኛ መጾሻ ሆነን በአንድነት ዋልታና ማገር የታነጸችውን ሀገራችንን ለማፍረስ መንፈራገጥ የለብንም። ቤታችን እንዳትጠበን በነፍሳችን ላይ የፍቅርን እሳት መለኮስ ግድ ይለናል። ብሄር ስም የምንለኩሰው እሳት መጀመሪያ እኛን ነው የሚያቃጥለን። መርዝ መጀመሪያ ብልቃጡን እንደሚጎዳ ሁሉ ክፉ ሀሳብም መጀመሪያ ባለቤቱን ነው የሚጎዳው።

ለማይጠቅመን ነገር መሮጥ ትተን በሚበጀን ነገር ላይ እንልፋ። አሁን የሚጠቅመን በጋራ ሀገር ማሳደግ ነው። ከአለም ድሀ የሆነችውን ሀገራችንን ማልማት፣ ማሰልጠን ነው። አሁን የሚጠቅመን በቀን ሶስት ጊዜ መብላት ያልቻለ ማህበረሰባችንን መታደግ ነው። የፖለቲካ ቅራኔዎችን በእርቅ መፍታት ነው። በዘር ተኮር ፖለቲካ ያጣናቸውን በረከቶቻችንን መፈለግ ነው። አሁን የሚጠቅመን ለወጣቱ የስራ እድል፣ ለዜጎች ደግሞ ምቹ ሀገር መፍጠር ነው። ህጻናት የሚያድጉባትን፣ አዛውንቶች የሚጦሩባትን ሀገር መገንባት ነው። አሁን የሚጠቅመን ትውልዱ የሚኮራበትን የጋራ እሴት መፍጠር ነው። በእርቅ ደም ማድረቅ ነው። በመነጋገር ችግሮቻችንን መፍታት ነው። አሁን የሚበጀን የዘር ፖለቲካ ያጠየመውን ኢትዮጵያዊነት ማስተካከል ነው። እኔነት አረም የበቀለበትን ሰውነታችንን ማከም ነው። እንዲህ ካልሆንን ንጋት አናይም። ኩርፊያና ጥላቻ ባጨለሙት ማምሻ ላይ ቆመን ንጋት መናፈቅ ሞኝነት ነው። መጀመሪያ ልቦቻችንን ለብርሀን እናዘጋጅ። መጀመሪያ አይኖቻችን ንጋት እንዲናፍቁ እናድርግ። በመጠላላት የመሹብን ንጋቶች፣ በዘር እሳቤ የዘገዩብን ተስፋዎች ከእርቅ በኋላ የሚነጉ ናቸው። እንዲነጋልን መታረቅ አለብን። መግባባት አለብን።

እስከመቼ በማይጠቅመን ነገር ላይ እየለፋን እንኖራለን? እስከመች አንድ ቦታ እየረገጥን እንደ ቀንድ አውጣ ስናዝግም እንኖራለን? የማይጠቅሙንን ስንከተል የሚጠቅሙን እያጣን እንደሆነ ቢገባን እላለው። አሁን ላይ ከገቡን ይልቅ ያልገቡን ብዙ ናቸው። የገቡን ይሄን ያክል ካሰቃዩን ያልገቡን ጠቃሚዎቻችን እንደሆኑ መረዳት አይከብደንም። እስኪ የገቡንን ትተን ወዳልገቡን እንራመድ። ያልገቡን በረከቶቻችን ስለመሆናቸው ገብተውን ካሰቃዩን መከራዎቻችን መረዳት እንችላለን። ያልገቡን ቢገቡን ኖሮ በዚህ ልክ ዋጋ ባልከፈልን ነበር። ገብቶናል ባልነው እኔነት፣ ገብቶናል ባልነው የብሄር ፖለቲካ ለዘመናት ተሰቃይተናል። አሁንም እየተሰቃየን ነው። ገብቶናል ባልነው ዘረኝነት፣ ገብቶናል ባልነው ሀይማኖተኝነት የዘመናት እሴቶቻችንን አጥተናል። እስኪ ወዳልገቡን ደግሞ እንመለስ.. እስኪ ወዳልተረዳነው እውነት እንመልከት። ምናልባት እኮ እነዛ ያልገቡን እውነቶች የመከራዎቻችን መፍትሄዎች ይሆናሉ። የህይወታችን አቅጣጫ ጠቋሚዎች ሊሆኑን ይችላሉ። ገብተውናል ባልናቸው ግን ደግሞ ባልገቡን ነውሮቻችን መሰቃየታችን ይብቃ። ያልገባን ፍቅር ነው..ያልገባን እኮ አንድነትና መቻቻል ነው። ያልተረዳነው እውነት ኢትዮጵያዊነት ነው። እስኪ ወዳልገቡን የፍቅርና የአንድነት መንፈሶች ዞር ብለን ደግሞ እንሞክረው። እስኪ ወዳልገባን ኢትዮጵያዊነት ተመልሰን ሰላማችንን እንፈልገው፣ ሞታችንን፣ ጉስቁልናችንን እንታደገው። ወዳልተረዳነው ዞረን በፍቅር ሞታችንን እንግደለው እላለው።

ተበልጠናል..ብሄርተኝነት ወልዶ ባሳደገው ምናምንቴ ጭንቅላት ስናስብ ተበልጠናል። የዘር ፖለቲካ ዘርቶ ባበቀለው ሰውነት ስንመጻደቅ ተበልጠናል። ጥላቻና ዘረኝነት ባስጎነበሰው ጎባጣ ጀርባና ትከሻ እየተራመድን ተበልጠናል። አሁን ሁሉም በልጠውናል። በሁሉም ተበልጠናል። ተለያይተን የተራመድንባቸው እነዛ የመጠላላትና የመገፋፋት ዘመኖች ዛሬ ላይ በብዙ ነገር ወደ ኋላ አስቀርተውን ለውጥ ናፋቂዎች አድርገውናል። ከአለም እኩል ለመሆን፣ ከአፍሪካ እኩል ለመቆም፣ ከጎረቤቶቻችን እኩል ለመሆን ዘረኝነትን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መቅበር አለብን። እንደሚታወቀው ሩዋንዳውያን በብሄር ፖለቲካ መጥፎ ታሪክ ያላቸው ህዝቦች ናቸው። አሁን ላይ በሩዋንዳ ምድር ከሩዋንዳ በቀር ሌላ ብሄር አይጠራም። እኛም ይሄን የዘር ፍጅት ለማስቆም ከሩዋንዳ የምንኮርጀው ብዙ ነገር ሊኖር ይገባል ባይ ነኝ። ከኢትዮጵያ በቀር የምናውቀው ሌላ ስም ሊኖረን አይገባም። በዘር ፍጅት ታሪኳን ያጣችው ሩዋንዳ ዛሬ ላይ ያን ጊዜ ላለማስታውስ እኛ ሩዋንዳዊ ነን የሚሉ ናቸው። በሩዋንዳ ምድር ከሩዋንዳ በቀር ሌላ ብሄር የሚጠራ ዜጋ ዘብጥያ ከመውረድ በቀር አማራጭ የለውም። ይሄ ደግሞ ምዕራፍና አንቀጽ ሰጥታ በህገመንግስቷ የደነገገችው እውነት ነው። እንደ ሩዋንዳ ማናችሁ ስንባል እኛ ኢትዮጵያዊ ነን ስንል የምንመልሰው የአንድነትና የኩራት ስም ያስፈልገናል። እንደ ሀገር አንድ ሆነን መቆም ካለብን ኢትዮጵያ የሚለው ስም ያስፈልገናል። ከአማራና ኦሮሞ፣ ከትግሬና ጋሞ በፊት የምንጠራው..የምንኮራበት ኢትዮጵያዊ ማንነት ግድ ይለናል።

ከዘር ፖለቲካ ወጥተን በፍቅር የምንሞትባት ኢትዮጵያ ናፍቃኛለች። ሰው እኮ በፍቅር ይሞታል..ሰው እኮ ሌላውን በማፍቀር፣ ለሌላው በመኖር ይሞታል። ነፍስ እኮ ስለሌሎች ስቃይ ታልፋለች። በኢትዮጵያ ምድር የናፈቀኝ ይሄ ነው..በፍቅር መሞት። እስኪ በጥላቻ መሞት ቀርቶብን በፍቅር እንሙት። እስኪ በመዋደድ እንሙት፣ እስኪ በሌሎች መከራ፣ በሌሎች ስቃይ፣ በሌሎች ጉስቁልና እንሙት። በጥላቻ መሞት ስንችል በፍቅር መሞት እንዴት አቃተን? እስካሁን ገለን የምንሞት ነን፣ ጠልተን የምንሞት ነን። እንደ እየሱስ አፍቅሮ መሞት እንዴት ተሳነን? የሚበጀን ይሄ ነው። የሚበጀን በፍቅር መሞት ነው። እናም ከጥላቻ ወጥተን በፍቅር እንሙት እላለው። ህዝብ ለሀገር ሲሞት ሀገር ለህዝብ ትሞታለች። አንዱ ለአንዱ ሲታመም ሰውነት ያኔ ዋጋ ያወጣል። ያኔ ነው ሀገርና ህዝብ፣ ትውልድና ታሪክ እረባና የሚኖራቸው። ያኔ ነው እንደ ሀገር ወደ ፊት ለመሄድ ብርታት የምናገኘው። በፍቅር እንሙት.. በሌሎች ስቃይ እንሰቃይ። የሌሎች ህመም ይመመን። የወገን ጉስቁልና ይሰማን..የፍቅር ሞት ያልኳችሁ ይሄንን ነው። እኔ በእናንተ ስታመም፣ እናንተ በእኔ ስትታመሙ ያኔ ሀገርና ህዝብ ትርጉም ያገኛል። የፍቅር ሞት ያልኳችሁ ይሄንን ነው። በአንዱ ውስጥ የአንዱ መብቀልን።

የፍቅር ሞት ህመም የለውም። የአንድነት ሞት ሞቶቻችንን ሁሉ የምንገልበት ጥበብ ነው። አሁን ላይ እየሞትን ያለነው በጥላቻ ሞት ነው። የጥላቻ ሞት ደግሞ ሌላ ሞት ይፈጥራል እንጂ ህይወት አይሰጥም። ሞቶቻችን የጥላቻዎቻችን ጽንሶች ናቸው። በዘር የፈጠርናቸው፣ በብሄር የጸነስናቸው ፋንድያዎች። የጥላቻ ሞት ትንሳኤ የለውም። የጥላቻ ሞት ዳግም ህይወትን አይሰጥም። በፈጣሪ ፊት በክብር አያስቆምም። ከፍቅር ርቀን ጠልተን ስንሞት በዚህኛውም አለም ሆነ በዚያኛውም አለም ትንሳኤ የለንም። ትንደሳኤ ያላቸው ነፍሶች በፍቅር ኖረው በፍቅር ያለፉ ናቸው። እናም እንዲህ እላችኋለው ስለሌላው በመኖር፣ ስለሌላው በማሰብ፣ ስለሌላው በመጨነቅ በፍቅር እንሙት። ያኔ ሌላ እንሆናለው..አሁን ከሆንነው ሌላ።

ሀገራችን ኢትዮጵያ የብዙ ጥበቦች መገኛ ሀገር ናት። ሌላው ሀገር ሰላም ሲያጣ፣ አንድነት ሲርቀው ወደ ኢትዮጵያ ነበር የሚመለከተው። ኢትዮጵያን የሰላም ቀንዲል፣ የአንድነት ዋርካ አድርገው ሀርና ህዝብ የመሰረቱ በርካቶች ናቸው። ሀገራችንን ተስፋ አድርገው፣ ህዝባችንን ተማምነው ሀገር የሆኑ እልፍ ናቸው። ዛሬ ይቺ ብዙዎችን ያስጠለለች ዋርካ ሀገራችን ዛፍ መሆን ባልቻሉ ሀገራትና ግለሰቦች ሰላሟን ስታጣ ማየት ጥያቄን ይፈጥራል። ለሌሎች ተርፎና ተትረፍርፎ ለራስ መላ ማጣት ህመሙ በምን ቃል እንደሚገለጽ አላውቅም። ሌሎችን ሀገርና መንግስት ያደረገች ቀዳማይት ምድር ዛሬ ዘመን ባለፈባቸው ነውረኛ ድርጊቶች ስትናጥ ማየት ከማስገረም ባለፈ ምን ሊባል ይችላል? አፍሪካን አንድ ያደረገች ሀገር ዛሬ ላይ በወንድማማቾች ደም ስትታጠብ ማየት ከማስቆጨትም በላይ ያማል።

ሀገሩን የሚወድ ሁሉ በእርቅ ደም ያድርቅ። በፍቅር ጥላቻን እንዲገድል አደራ እላለው። በዚች ሀገር ብዙ የተማጽኖ አደራዎች ተሰምተዋል። ብዙ የይቅር፣ ብዙ የእርቅ ድምጾች አስተጋብተዋል። አባቶች ተናግረዋል፣ የሀይማኖት መሪዎች አደራ ብለዋል ግን ካልገቡን ይልቅ የገቡን ልቀው ጆሮ ዳባ ብለን በራሳችን ላይ መከራ ፈጥረናል። ካልተረዳናቸው መንፈሶች ይልቅ የተረዳናቸው የጥፋት እውነቶች ሚዛን ደፍተው ጸዳሎቻችንን ነጥቀውናል። እኔም አደራ እላለው.. በእርቅ ደም እንዲደርቅ፣ በፍቅር ሞት እንዲቀር አደራ እላለው። የሚበጀን ይሄ ነው..በእርቅ ደም አድርቀን፣ ይቅር ለእግዜር ተባብለን ወደ ፊት መራመድ። መች እንደሚበቃን አላውቅም..ሀገር ፈርሳ መግቢያ ያለን ይመስል፣ ወገን ከድተን መጠጊያ ያለን ይመስል የጥፋት ሩጫችን ይገርማል። በዚች ሀገር ላይ ያልገቡን እንዲገቡን አደራ እላለው። ከፍቅር በቀር፣ ከአንድነት በቀር ሁሉም የገባን ህዝቦች ነን። ያልገቡን እንዲገቡን ልባችንን እንክፈት እያልኩ ላብቃ።

> **በጥላቻ መሞት ስንችል በፍቅር መሞት እንዴት አቃተን? እስካሁን ገለን የምንሞት ነን፣ ጠልተን የምንሞት ነን። እንደ እየሱስ አፍቅሮ መሞት እንዴት ተሳነን? የሚበጀን ይሄ ነው። የሚበጀን በፍቅር መሞት ነው። እናም ከጥላቻ ወጥተን በፍቅር እንሙት እላለው። ህዝብ ለሀገር ሲሞት ሀገር ለህዝብ ትሞታለች**

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## ለነዳጅ ምርትና ለአካባቢ ጥበቃ ድርብ ተስፋ የተጣለበት የፈጠራ ሥራ

**አንተነህ ቸሬ**



የምሩቃኑ የፈጠራ ውጤት የሆነው ፕላስቲክን ወደ ነዳጅ መቀየር የሚያስችለው ቴክኖሉጂ

የፈጠራ ሥራዎች ለአገራዊ እድገትና ለመዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግር እውን መሆን ተስፋ የሚጣልባቸው ወሳኝ ግብዓቶች እንደሆኑ ይታመናል። የፈጠራ ሥራዎቹ አገር በቀል ሲሆኑ ደግሞ ፋይዳቸው እጥፍ ድርብ ይሆናል። እነዚህ ሥራዎች አገራዊ የአምራችነት አቅምን በማሳደግና ለኅብረተሰቡ ችግሮች ዘላቂ መፍትሄ በመሆን በአገር እድገት ላይ ጉልህ አዎንታዊ ሚናም ይጫወታሉ።

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች የሚከናወኑ የፈጠራ ሥራዎች ተማሪዎች በንድፈ ሃሳብ የጨበጡትን ግንዛቤ በተግባር የመተርጎም ብቃታቸውንና ዝግጁነታቸውን ይጠቁማሉ። ይህም ከተቋማቱ የሚመረቁ ተማሪዎች ሥራ ፈጣሪ እንዲሆኑ፣ የአምራች ዘርፉ አቅም እንዲጎለብትና የአገር ምጣኔ ሀብት እንዲጠናከር ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ያግዛል። በዚህ ረገድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ከላይ የተጠቀሱትን ግቦች ለማሳካት የሚያግዙ የፈጠራ ሥራዎችን እውን ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች እየተረዳን ነው።

በቅርቡ ከጅማ ዩኒቨርሲቲ በሜካኒካል ምህንድስና (Mechanical Engineering) የትምህርት ዘርፍ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ያገኙ ስድስት ተመራቂዎችም ነዳጅን በቀላሉ ለማምረት የሚያስችል የፈጠራ ሥራ መሥራት ችለዋል። የፈጠራ ሥራውን ከሠሩት ተመራቂዎች መካከል አንዷ ስምረት ጴጥሮስ ትባላለች። ስምረት እንደምታስረዳው፣ የፈጠራ ሥራው ፓይሮላይሲስ (Pyrolysis Process) በተባለ ዘዴ አገልግሎት የማይሰጡ የፕላስቲክ ውጤቶችን ወደ ነዳጅ ምርት ለመቀየር የሚረዳ የቴክኖሎጂ ውጤት ነው። ፓይሮላይሲስ ያለምንም አክስጅን፣ ሙቀትን ብቻ በመጠቀም የፕላስቲክ ውጤቶች ወደ ነዳጅ ምርት የሚቀየሩበት ቴክኖሎጂ ነው።

ተመራቂዎቹ የፈጠራ ሥራውን ለመሥራት ያሰቡት ለመመረቂያ ጽሑፋቸው ሲሆን ጊዜያቸውን በአግባቡ ለመጠቀም የወረቀት/ጽሑፍ እና የተግባር/የናሙና (Prototype) ሥራውን ተከፋፍለው ያከናውኑ ነበር። የፕሮጀክቱ አማካሪ መምህር ኣብርሃ ካህሳይም በየቀኑ፣ ከተመራቂዎቹ ጋር በመገኘት እያንዳንዱን ሥራቸውን እየተመለከቱ ክትትል አድርገውላቸዋል።

በፓይላይሲስ ቴክኖሎጂ ሁሉንም ዓይነት የፕላስቲክ ውጤቶች ወደ ነዳጅ መቀየር ይቻላል። ተመራቂዎቹ ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ አንዳንድ የፕላስቲክ ዓይነቶች የቴክኖሎጂውን ቱቦ እየደፈኑ ያስቸግሯቸው እንደነበር በማስታወስ ‹‹በዘርፉ የተሻለ እውቀትና ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች በሥራው ሂደት የሚሳተፉ ከሆነ የፕላስቲክ ውጤቶችን ወደ ነዳጅ የመቀየር ውጤታማነት ማሳደግ ይቻላል›› ትላለች።

እንደ ስምረት ማብራሪያ፣ ማሽኑ የተሠራው በዩኒቨርሲቲው ግቢ ከሚገኙ ዕቃዎች ነው፤ ከውጭ የተገዛ ዕቃ የለም። ለምርቱ የሚያስፈልጉትን ማምረቻዎች ለመሥራት፣ ብረታ ብረቶችን እንዳስፈላጊነቱ በማጠፍና የተለያዩ ዓይነት ቅርፆችን በመስጠት፣ ዲዛይን ከተደረገ በኋላ ለምርቱ የሚፈለገውን ቅርፅ በማስያዝ ተሠርቷል።

እነ ስምረት ሃሳቡን አደራጅቶና ወደ ተግባር ለውጦ ለማጠናቀቅ ከአንድ ወር በላይ ፈጅቶባቸዋል። በእነዚህ ጊዜያትም ተመራቂዎቹ በየቀኑ እየተገናኙ ይሠሩ ነበር። ‹‹ሁሉም ነገር የተሟላለት ነው›› ባይባልም የዩኒቨርሲቲው ላቦራቶሪ ባለው አቅም በመታገዝ ሥራቸውን አከናውነዋል። የተመራቂዎቹ ምርት ጥቅም ላይ መዋል የሚችል ነዳጅ እንደሆነም ተረጋግጧል፤ በተሻለ የግብዓት አቅርቦት የተሻለ ምርት ማግኘት እንደሚቻልም ምክረ ሃሳባቸውን አስቀምጠዋል።

ስምረት ‹‹ርዕሰ ጉዳዩን የመረጥነው ከመመረቂያ ጽሑፍነት የዘለለ ትርጉምና ፋይዳ ስላለው ነው። በአሁኑ ወቅት የነዳጅ ፍላጎት መላው ዓለምን የሚመለከት ወሳኝ ጉዳይ እንደሆነ ይታወቃል። በተለይ ደግሞ የአገራችንን ኢኮኖሚና እንደ ግለሰብ እያንዳንዳችንንም በደንብ የሚነካ ጉዳይ ሆኗል። ስለሆነም ጉዳዩ ከመመረቂያ ጽሑፍነት የሚያልፍ በመሆኑ ወደ ቢዝነስ ተቋም (Startup Company) በማሳደግ ሥራውን በትልቅ መጠን ለማከናወን እቅድ አለን።›› በማለት ታብራራለች። ይህን ለማሳካት ደግሞ ሥራውን በተሻለ መጠንና ጥራት ለማከናወን የሚያስችሉ ጥናቶችንና ዝግጅቶችን ማድረግ እንደሚፈልግም ትናገራለች። የፈጠራ ሥራው ነዳጅን ከማምረት በተጨማሪ የወዳደቁ የፕላስቲክ ውጤቶችን ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል መሆኑንም ጠቅሳ፣ ‹‹በቀጣይ ምን ማድረግ እንዳለብን እየተነጋገርን እንገኛለን›› በማለት ታብራራለች።

ተመራቂዎቹ ሥራቸውን ሲያከናውኑ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ልዩ ልዩ ድጋፎችን አድርጎላቸዋል። ‹‹ጅማ ዩኒቨርሲቲ ዕቃዎችን አቅርቦልናል። በፈለግነው ጊዜ እየሄድን እንድንሠራ የላብራቶሪ አቅርቦትም አመቻችቶልናል። በላብራቶሪ ውስጥ ስንሠራ ለመቁረጥና ለመበየድ የሚያስፈልጉ ማሽኖችን ለሥራችን ፈቅዶልናል። በአጠቃላይ ዩኒቨርሲቲው ማቅረብ የሚችለውን ዕቃ አቅርቦልናል። ሁሉንም ሥራ ያከናወንነው ግቢው በሰጠን ማቴሪያሎች ነው›› በማለት ስምረት ዩኒቨርሲቲው ስላደረገላቸው ድጋፍ ገልፃለች።

በሌላ በኩል ‹‹ምን ትፈልጋላችሁ?›› ብለው ለጠየቋቸው አካላት የሚያስፈልጋቸውን እገዛ እንዳሳወቁም ነው የምትናገረው። እስካሁን ድረስ በይፋ ድጋፍ የሚያደርግ አካል ባይገኝም በቀጣይ ጊዜያት ግን የፕሮጀክት ሃሳቡ አሁን ካለው የበለጠ ዳብሮና ተስተካክሎ ሲዘጋጅ ድጋፍ የሚያደርጉ አካላት ይገኛሉ ብለው ተስፋ ያደርጋሉ። ለጊዜው የፈጠራ ሥራቸው የሚጠራበትና የፈጠራ ባለቤቶቹም የሚታወቁበት የቡድን ስያሜ ባይኖራቸውም፣ ሥራቸውን በማሻሻልና ለቡድናቸውም ስያሜ ለመስጠት እንደሚያስቡም ስምረት ጠቁማለች።

የተመራቂዎቹን የፈጠራ ሥራ በአማካሪነት የመሩት በጅማ ዩኒቨርሲቲ የሜካኒካል ኢንጂነሪንግ መምህር አብርሃ ካህሳይ፣ ፓይሮላይሲስ አንድን ዕቃ ያለኦክስጅን በሙቀት የማቃጠል ሂደት መሆኑን ገልጸው፤ የተመራቂዎቹ ፕሮጀክትም የፕላስቲክ ውጤቶችን ያለምንም ኦክስጅን በሙቀት በማቃጠል የነዳጅ ምርት ማስገኘት የቻለ የፈጠራ ውጤት እንደሆነ ያስረዳሉ።

እርሳቸው እንደሚሉት፣ የፈጠራ ሥራው ነዳጅን ከማምረት በተጨማሪ ሌሎች ዓላማዎችንም የሚያሳካ ፕሮጀክት ነው። አንደኛው አካባቢን የሚበክሉ ፕላስቲኮችን ለነዳጅ ምርት ግብዓት በመጠቀም ወደ ጥቅም መቀየር ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ የግብርና ተረፈ ምርቶች ፕላስቲኮችን ለማቃጠል ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ ነው።

የተመራቂዎቹ የፈጠራ ሥራ ከነዳጅ ምርት የተሻገረ ተጨማሪ ፋይዳም አለው። ቴክኖሎጂው የወዳደቁ የፕላስቲክ ውጤቶችን በመሰብሰብ ለምርት ሥራ የሚጠቀም በመሆኑ የፕላስቲክ ውጤቶች በአካባቢ ብክለት ላይ የሚኖራቸውን ድርሻ ለመቀነስና ሥነ ምኅዳርን ለመጠበቅ ያግዛል።

የፈጠራ ሥራው አሁን ከተገኘው በተሻለ መልኩ ከተሠራ፤ በነዳጅ አቅርቦት እና በአካባቢ ጥበቃ ዘርፎች ያሉትን አገራዊ ውስንነቶች ለማቃለል አስተዋፅኦ እንደሚኖረው የፈጠራ ሥራው ባለቤቶች ተስፋ ያደርጋሉ። በተመራቂዎቹ አማካኝነት የተሠራውን ቴክኖሎጂ በመጠቀም ነዳጅን በብዛት ማምረት ከተቻለ በነዳጅ እጥረት ምክንያት የሚጋጥሙ ችግሮችን መቅረፍና ምርታማነትን ማሳደግ እንዲሁም አገሪቱ ለነዳጅ የምታወጣውን ወጪ መቀነስ ብሎም ማስቀረት እንደሚቻል ያምናሉ። ከዚህ በተጨማሪም የፈጠራ ሥራው አካባቢን በመበከል ችግር የሚፈጥሩ የፕላስቲክ ውጤቶችን ለነዳጅ ምርት ግብዓት እንዲሆኑ በማድረግ የችግር መፍትሄ እንጂ ችግር እንዳይሆኑ የማድረግ አቅምም እንደሚኖረው ተስፋ ተጥሎበታል።

‹‹ፓይሮላይሲስ ቴክኖሎጂ ኢትዮጵያ ውስጥ በብዛት ጥቅም ላይ አልዋለም እንጂ በሌላው ዓለም አዲስ ቴክኖሎጂ አይደለም›› የምትለው ስምረት፣ ነዳጅን የማምረት ፈጠራቸው ችግር ፈቺ ተግባራት ላይ ማተኮር እንደሚያስፈልግ ካላቸው እምነት የሚመነጭ እንደሆነ ትገለፃለች። ‹‹ፓይሮላይሲስ ቴክኖሎጂ አዲስ ቴክኖሎጂ አይደለም። የፕላስቲክ ውጤቶችን ለድጋሚ አገልግሎት ጥቅም ላይ ማዋልም የተለመደ ቢሆንም፣ ከዚህ ቀደም የፕላስቲክ ውጤቶች ለድጋሚ አገልግሎት ጥቅም ላይ የሚውሉት ተመሳሳይ ምርቶችን ለማምረት ነው። ‹ይህኛው ሥራ አሁን ለምን አስፈለገ› ብለን ብንጠይቅ ችግር ፈቺ መሆን ስላለብን ነው። ሃሳባችን አሁናዊ ችግራችንን የሚቀርፍ ከሆነ ትኩረታችንን መሰል ተግባራት ላይ አድርገን መሥራትና መጠቀም ይኖርብናል›› በማለት ታስረዳለች።

ስምረት እንደምትለው፣ ፓይሮላይሲስ ቴክኖሎጂ ኢትዮጵያ ውስጥ በስፋት ጥቅም ላይ ካለመዋሉ በተጨማሪ ቴክኖሎጂውን መጠቀም የጀመሩት ሌሎች አገራትም ፕላስቲኩን ለማቃጠል የሚያስፈልገው የነዳጅ ወጪ ከፍተኛ ሆኖባቸው በፈለጉትና ባቀዱት ልክ ሊቀጥሉበት አልቻሉም። ተመራቂዎቹ የፈጠራ ባለቤቶች ይህን የነዳጅ ወጪ ለማስቀረት የተጠቀሙት ዘዴ ነዳጅን ተክተው ፕላስቲክን ለማቃጠል የሚውሉ እንደቡና ገለባ ያሉ ሌሎች ምርቶች ተረፈ ምርቶችን መጠቀም ነው።

‹‹ተመራቂዎቹ በፈጠራ ሥራቸው ያመረቱት ነዳጅ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል እንደሆነ በሙከራ ታይቷል›› የሚሉት መምህር አብርሃ፣ የፈጠራ ሥራው ተጨማሪ የማጣራት ሂደቶችና የማሻሻያ ሥራዎች የሚከናወኑለት ስለሆነም ምርቱ በአጭር ጊዜ ወደ ገበያ ለመቅረብ እንደማይችል ያስረዳሉ። ‹‹ሌሎች የማጣራት ሂደቶችና ጥናቶች ያስፈልጉታል። ለምሳሌ ያህል የፕላስቲክ ውጤቶቹ በሙቀት በሚቀልጡበት ወቅት የሚፈጠረው ትነት ውሃ እንዲፈጠር ስለሚያደርግ ውሃውን ከነዳጁ መለየት ያስፈልጋል። አሁን ባለን የላቦራቶሪ አገልግሎት ይህን ማድረግ አልተቻለም። አሁን ባለበት ደረጃ በአንድ ጊዜ ወደሚፈለገው ደረጃ (Standard) ከፍ ማድረግ ስለማይቻል በቀላሉ በብዛት ወደ ገበያ ለማቅረብና እርግጠኛ ሆኖ ለመናገር ከባድ ይሆናል።›› ሲሉ ያብራራሉ።

ስምረት በበኩሏ ‹‹እኛ የሠራነው በትንሽ መጠን ነው። ሥራው ጊዜ ይፈልጋል። ምርቱ ወደ ገበያ ለመውጣት በብዛት መመረት አለበት። ለዚህ ደግሞ ፕላስቲክ ውጤቶችን በብዛት መሰብሰብና ማቃጠል፣ ለማምረት የሚፈጀውን ጊዜ ማሳጠር እንዲሁም ማሽኑ በብዛትና በፍጥነት እንዲያመርት የሚያስችሉ ማሻሻያዎችን ማድረግ ያስፈልጋል። በተጨማሪም ምርቱን በትልቅ ቦታ ላይ ማምረትም አስፈላጊ ነው። እነዚህ ግብዓቶችና ቅድመ ሁኔታዎች ከተሟሉ ምርቱን በተሻለ ጥራና ብዛት ለገበያ ማቅረብ ይቻላል። እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ካልተሟሉ ምርቱን በተሻለ ጥራት፣ ፍጥነትና ብዛት ለገበያ ለማቅረብ የሚደረገውን ጥረት ያጓትተዋል›› ትላለች።

የተመራቂዎቹን የፈጠራ ሥራ ከዳር ለማድረስና ምርቱን በተሻለ ጥራትና መጠን ለገበያ ለማቅረብ የሚደረገውን ጥረት ለማሳካት ዩኒቨርሲቲው የፈጠራው ባለቤቶች ጥናታቸውን እንዲቀጥሉ የሁለተኛ ዲግሪ የትምህርት ዕድል እንደሰጣቸውና ፕሮጀክቱን የሚደግፉ አካላትን ለማፈላለግ ጥረት እየተደረገ መሆኑንም መምህር አብርሃ ተናግረዋል።

ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያውያን ስለተሠሩ በርካታ የፈጠራ ሥራዎች በተደጋጋሚ ሲነገር ሰምተናል። ይሁን እንጂ እነዚህ የፈጠራ ሥራዎች በጥራትና በብዛት ተመርተው፣ ለገበያ ቀርበው ለኅብረተሰቡ ዘላቂ መፍትሄ ሲሆኑ የምንመለከትበት አጋጣሚ ግን ብዙ አይደለም።

ዛሬ በምጣኔ ሀብታቸው የዓለም ቁንጮ የሆኑት አገራት ለዚህ ደረጃ የበቁት በአምራችነታቸው ምክንያት ነው። ስለሆነም በኢትዮጵያም በየጊዜው ለሚሠሩ የፈጠራ ሥራዎች እገዛ በማድረግ የአገሪቱን ምጣኔ ሀብት ትርጉም ባለው መጠን መደገፍና ማሳደግ ያስፈልጋል።

## ወቅታዊ ትንታኔ

# የኢትዮጵያ ባንኮች የውጭ ባንኮችን ተወዳዳሪ እንዲሆኑ

**አስቴር ኤልያስ**

በኢትዮጵያ አዳዲስ ባንኮች ዘርፉን እየተቀላቀሉ እንደሆነ ይታወቃል። በቅርቡም ዘርፉን ከተቀላቀሉት ውስጥ አማራ ባንክና የፀሐይ ባንክ ተጠቃሽ ናቸው። በአማራ ባንክ ይፋዊ የሥራ ማስጀመሪያ ሥነ ሥርዓት ላይ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥ ዶክተር ይናገር ደሴ፣ የኢትዮጵያ ባንኮች ከውጭ ባንኮች ጋር ለሚኖረው ውድድር ራሳቸውን ከወዲሁ እንዲያዘጋጁ ጥሪ አድርገዋል።

የባንኮች ቁጥር እያደገና የቅርንጫፍ አገልግሎት መስጫቸውም እየተስፋፉ ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ያለው የባንክ ኢንዱስትሪ አሁን ባለበት ሁኔታ የመወዳደር አቅሙ እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነው። በመሆኑ ለውድድር ብቁ ይሆን ዘንድ የአገልግሎት ልህቀት ሊኖረው እንደሚገባ የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ዛፉ ኢየሱስወርቅ ዛፉ ይገልጻሉ።

እርሳቸው እንደሚሉት፤ በመጀመሪያ የአገራችን ባንኮች ትክክለኛ ውድድር ምን እንደሆነ በተለይ ከአጼ ኃይለሥላሴ ወዲህ የማናውቀው ነገር ነው። የመወዳደር አቅም ሲባል ግን መለኪያው የአገልግሎት ልህቀት ነው። የአገልግሎት ልህቀት ደግሞ የሚያካትተው ሁሉንም ነገር ነው። ለአብነት ያህል በመጠን፣ በዓይነት፣ በጥራት እንዲሁም በጊዜ የሚለካው ሁሉ የአገልግሎት ልህቀት ነው። ለተገልጋዩ መስጠት የሚገባው አገልግሎት እነዚህን የተጠቀሱትን መስፈርት በማሟላት ነው።

ይህ የመጣው ከዚህ አገር ነው፤ ይህኛው እምነቱ እንዲህ ነው፤ ያኛው ደግሞ ትውልዱ ከወዲያ ነው በሚል የሚሠራ አይደለም። ባንክ ከሆነ በባንክ ሥራ ከሁሉም የተሻለ ለተጠቃሚ አገልግሎት መስጠት የሚችል መሆን አለበት። በዚህም መሠረት ጥሩ አገልግሎት በተመጣጣኝ ዋጋ የሚሰጥ ውድድሩ ከሚያሳድርበት ተጽዕኖ ነፃ ከመሆኑም በተጨማሪ አሸናፊ ነው። ውድድር የሚያመጣበትን ተጽዕኖ መቋቋም የሚችለው እንደእርሱ ባንክ ነው።

በመጀመሪያ ደረጃ የኢትዮጵያ የባንክ ኢንዱስትሪ ቢከፈት እዚህ አገር መጥተው የሚወዳደሩት (አንዳንድ ሰዎች ይመጣሉ ብለው የሚያስቡት) ግዙፎቹን ባንኮች ነው፤ ነገር ግን እንደሱ ሳይሆን ከሁሉ አስቀድሞ ከጎረቤት አገር ከኬንያ ሊመጣ እንደሚችል መረዳት ተገቢ ነው። ከእነዚህ ቀጥሎ ደግሞ እስካሁን ድረስ ከአገራቸው ውጪ እየሠሩ ያሉ የናይጄሪያና የደቡብ አፍሪካ ባንኮች አሉ። ስለዚህ አብዛኛዎቹ ምናልባት ከሰሜን አፍሪካ፣ ከሞሮኮ ሊመጡ የሚችሉ ይኖሩ ይሆናል። እነዚህ ባንኮች አንዳንዶቹ በአብዛኛው በአፍሪካ ኢንቨስተሮች የተያዙ ሊሆኑ ይችላሉ። ደግሞም ዓለምአቀፍ ግንኙነት ያላቸው ናቸው። ይህ ማለት ካፒታሊስት ዓለም ውስጥ ያሉ እንደ አሜሪካ፣ ካናዳ እና አውሮፓ አገር ውስጥ ያሉ ባንኮችም ሊመጡ ይችላሉ።

እኛ አገር ውስጥ እስካሁን ድረስ በዘርፉ እየተንጸባረቀ ያለው ሁኔታ የሚያሳየው አንደኛ ውድድርን የዘርና የኃይማኖት ወይም የትውልድ ጉዳይ ማድረግ ነው የሚሉት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው፣ ይህ በአደባባይ የሚታይ ነገር መሆኑን ይናገራሉ። ከዚህም አልፎ ውድድሩ የፖለቲካ መገለጫም ሆኗል ይላሉ።

‹‹እኔ ወደአገር ቤት ከመመለሴ በፊት በዚህ ጉዳይ ብዙ ሳወራ ቆይቻለሁ። አንዳንዴ ነገሩን ለማጣጣል በመንግሥት በኩል የሚጠቀሙባቸው ሁኔታዎች አሉ። እኔ ወደአገር ቤት ተመልሼ በዚህ ሥራ ውስጥ ከተሰማራሁ ወደ 30 ዓመት ገደማ ሆኖኛል። ለሦስት አስርት ዓመታት በተከታታይ ስናገር የነበረው ነገር ቢኖር አዲስ ስንቋቋም ምናልባት ለአምስት ዓመት እንዲያም ካለ ለአስር ዓመት እጅግ ይብዛ ከተባለ ደግሞ እስከ 15 ዓመት ድረስ የውጭ ተወዳዳሪዎች መጥተው እንዳይደፍቁን ትንሽ ከለላ ስጡን ብለን ነው። ይሁንና በዚህ ሁኔታ ድፍን 30 ዓመት ሊሞላን ነው። ስለዚህም የሚሰማን አጣን ይላሉ።

‹‹እኛ ያቺ አምስትም አስርም ወይም አስራ አምስትም ዓመት መንግሥት ከለላ የሚሰጥባትን ጊዜ አንደኛ ስለባንክ እውቅት፣ ስለባንክ ስልጡንነት እንድናካሂድ ነው። አንድ ባንክ ስናቋቁም ሁልጊዜ በብቸኝነት ሲሠራ ወደቆየው ወደንግድ ባንክ ሄደን የዲፓርትመንት ኃላፊ ወይም የአንድ ቅርንጫፍ ኃላፊ የሆነውን አባብለን አምጥተን ላቋቋምነው አዲስ ባንክ ሥራ አስፈጻሚ ማድረግ ነው። ነገር ግን እንደሱ ብቻ ማድረግ ሳይሆን በባንክ ሥራ በደንብ እየጎበዙ፣ እያወቁ፣ እየመጠቁ የሚሄዱ ኢትዮጵያውያንን ማፍራት ነው ያለብን።›› ሲሉ ይመክራሉ።

> **የኢትዮጵያ ባንኮች ከውጭ አገር ባንኮች የሚመጣባቸውን ትክክለኛ ውድድር ለመቋቋም አይቻላቸውም፡፡ ምክንያቱም ቴክኖሎጂውም፣ እውቀቱም፣ የገንዘብ ኃይሉም ወይም መጠኑም እስካሁን ድረስ የለም**

አቶ ዛፉ ኢየሱስወርቅ እንደሚናገሩት ከሆነ፤ እነርሱ ቀደም ሲል ሲጠይቁ የነበረው የስልጠና ሁኔታ እንዲፈጠር፣ አንዳንዶቹ ዩኒቨርሲቲዎች ደግሞ ለባንክ ወይም ለፋይናንስ ዘርፍ ሥራ ብቁ የሚያደርግ ትምህርትና ስልጠና እንዲሰጡ ማድረግ የሚለው ነበር።

አሁን ብሔራዊ ባንክ ለውድድር ራሳችሁን አዘጋጁ የሚል ከሆነ አንዱን ልጅ ሌላውን የእንጀራ ልጅ እያደረገ መሆን የለበትም የሚል ሀሳብ አላቸው። ሁሉንም በአንድ ዓይን እንዲያይና ለሁሉም እኩል ዕድል እንዲሰጥ ማድረግን መማር ይኖርበታል። ይህንን ቀደም ሲልም ተናግረናል። በእርግጥ ለዚህ ዓይነት ሁኔታ አገሪቱ አስቸጋሪ ናት። መንግሥት ራሱ የራሱ ባንክ አለው። ክልሎች የራሳቸው ባንኮች አሏቸው። ይህ በሆነበት ሁኔታ ብሔራዊ ባንክ እንዴት አድርጎ ነው ሁሉንም በእኩል ሊያይ የሚችለው። በጥቅሉ የማይቻል ነገር መጠየቅ ነው።

ስለዚህም የእኛን አገር ሁኔታ ያቆየነው አባጣ ጎርባጣ አድርገነው ነው። በመሆኑም ይህ ነገር እንዲህ እንዳይሆን ቀደም ብሎ አስፈላጊው ዝግጅት እንዲጀመር ነበር የተጠየቀው። ይህ ባለመሆኑ አሁን ያለንበት ቦታ ላይ ደርሰናል። አሁን ባለንበት ሁኔታ አገራችን ጥሩ ሒደት ላይ ናቸው የምንላቸው ቁንጮ ላይ የተቀመጡ ባንኮች ሦስት አራት ቢሊዮኑን እንኳን በቂ የመወዳደር አቅም የላቸውም።

ምክንያቱም የሚፈለገው ዓይነት የሰለጠነ የባንክ ባለሙያ በብዛት አያገኙም፤ የላቸውም። ልምዳቸውም ቢሆን የተወሰነ ዘመን ልምድ ነው። እስካሁንም ከአገሪቱ ውስጥ ካለው ጎጠኛ አስተሳሰብ ውስጥ ተጠቃሚዎች ናቸው። በመሆኑም ያለእሱ ጠንክረው ቆመው የውጭ ተወዳዳሪዎችን ተወዳድረው በገንዘብ አቅም፣ በእውቀት፣ በቴክኖሎጂ አሸንፈው ይወጣሉ ለማለት በጣም ያስቸግራል። ስለዚህ የአገራችንን ባንኮች ለውጭ ተወዳዳሪነት አላዘጋጀናቸውም።

ይህ ዝግጅት ባለመኖሩ የኢትዮጵያ ባንኮች ከውጭ አገር ባንኮች የሚመጣባቸውን ትክክለኛ ውድድር ለመቋቋም አይቻላቸውም። ምክንያቱም ቴክኖሎጂውም፣ እውቀቱም፣ የገንዘብ ኃይሉም ወይም መጠኑም እስካሁን ድረስ የለም። የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ለምን እንደዚህ ሆነ ለማለት አሁን ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ ይሆናል ይላሉ።

ይሁንና መንግሥት፣ ገበያውን ለውጭ ውድድር ክፍት እናደርጋለን ብሏል። እኛ ገበያውን ከውጭ ባንኮች ዘግተንላችሁ ነው እናንተ ይህን ጠርቀም ያለ ገንዘብ ስታገኙ የቆያችሁት እያለም በማስፈራሪያ መልክ ያቀርባል የሚሉት አቶ ዛፉ እየሱስወርቅ፣ በዚህ ጉዳይ ግን ስህተት ናቸው ብለዋል። ስህተት ነው የማለታቸውም ምስጢር የቀድሞ ሰዎች የሚሏቸውን እያዳመጡ ነው እንጂ ባንክ ውስጥ ያለነው ሰዎች ዘግታችሁ ይህን ያህል ዓመት ጠብቁ ወይም አኑሩ ባለማለታቸው እንደሆነ ይናገራሉ። እንዲያውም በባንክ ውስጥ ያሉ አካላት ቶሎ ተዘጋጅተውና ቶሎ ተወዳዳሪ ሆነው ገበያውም ተከፍቶ ማየትን ይናፍቁ እንደነበር ነው የገለጹት። ከዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ሆነው ከሚመጣው የውጭ አገር ውድድር ጋር ራሳቸውን በማሰለፍ አብረው እንዲሠሩና አቅማቸውን እንዲገነቡም ፍላጎታቸው እንደነበር ይናገራሉ።

እንደ ምጣኔ ሀብት ባለሙያው አባባል፤ ያለፈው ሁኔታ ግን ተዘግቶ የነበረው በፖለቲካ ምክንያት ነበር። በወቅቱ መንግሥት ይል የነበረው ገንዘቦች እኔ ባልኳቸውና እኔ በመረጥኳቸው አቅጣጫ እንጂ ኢንቨስተሮች በመረጡት አቅጣጫ እንዲሆኑ አልፈልግም ነው፤ ቅድሚያ የሚሆነውን ልማት የማዝበት እና የማውቀው እኔ ነኝ፤ ስለዚህ እኔ በምፈቅድበት ጊዜ ይከፈታል፤ እስከዛ ድረስ ግን እኔን የምትደግፉ ተጠቃሚ ትሆናላችሁ፤ መሥራት የምትችሉትም በእዛ መልክ ነው ብሎ በሩን ጥርቅም አድርጎ ዘግቶ ቆይቷል።

የለውጡ መንግሥት ከመጣ በኋላም እንዳየነው ባንኮች እየተጠሩ ይህን ያህል ብር ለዚህ ጉዳይ እርዳታ አድርጉ፤ ይህን ያህል ብር ደግሞ ለዚህ ጉዳይ አምጡ ይባላሉ። በሩ ተከፍቶ የውጪዎቹ ባንኮችም ገብተው እና ተወዳዳሪ ብንሆን ኖሮ መንግሥት የገቡትን ባንኮች እየጠራ ይህን ያህል ብር ለዚህ ጉዳይ፤ ይህን ያህሉን ደግሞ ለዛኛው ጉዳይ ማለት ይቻል ነበር ወይ ሲሉ ይጠይቃሉ። እንደዛ ማድረግ ግን በጭራሽ አይቻልም። ባንኮች ድጋፍ በሚፈልግበት ጊዜ የሚጠየቁት አገር በቀል ባንኮች በመሆናቸው ነው። ስለዚህ የባንኩ የሥራ ክፍል ለውጭ ተሰጥቶ ቢሆን ኖሮ ዓለምአቀፍ ባንኮቹ በዚህ መልኩ አይጠየቁም። በመሆኑም መንግሥት ለራሱም ሲል ነው ዘግቶት ያቆየው ይላሉ።

አሁን የባንክ ኢንዱስትሪው ለውጭ አገር ውድድር አይከፈት ማለት አይቻልም። የምንፈልገውም እንዲከፈት ነው፤ ስንጠይቅም ቆይተናል። አሁን ግን ያለንበት ሁኔታ ለዝግጅት ጊዜ በአጭሩም ቢሆን ትንሽ ስለሚያስፈልግ የውጭ ባንኮችን እዛው ውጪ ቆዩ በማለት ፈንታ በባለቤትነት መልክ ያሉ ባንኮች ውስጥ አክሲዮን እየገዛችሁ ግቡ ማለት ይቻላል። መቶ በመቶ በራሳችሁ ካፒታልና በራሳችሁ የሰው ኃይል ማቋቋም ሳይሆን በአገሪቱ ካሉ ባንኮች ጋር እየተወያያችሁና እየመረጣሁ ይበጁናል፤ አብረናቸው ልንሠራ እንችላለን ከምትሏቸው ባንኮች ጋር ካፒታል አክሲዮናቸውን በተወሰነ ደረጃ እየገዛችሁ አጋርነት ፍጠሩ ማለቱ ተመራጭ ነው። ለምሳሌ ለሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት እስከ 25 በመቶ፣ በሒደት ደግሞ እስከ 49 በመቶ ባለቤትነት መግዛት ትችላላችሁ ብሎ ሊፈቅድላቸው ይችላል። ይህ አንዱ የውጭ ባንኮችን ወደአገር ማስገቢያ ዘዴ ነው ይላሉ።

ይህ የተደረገ እንደሆነ አንደኛ የውጪ ካፒታል ይመጣል። እነዚህ የውጭ ባንኮች አገር ቤት ውስጥ ካሉት ባንኮች ጋር ባለቤትነትን ሲፈልጉ ከፍለው የሚገቡት በውጭ ምንዛሬ ነው። ስለሆነም የውጪ ካፒታል ይመጣል። እዚህ ሲመጡ ቴክኖሎጂውንና እውቀቱን ይዘው ይመጣሉ፤ ምክንያቱም ባለቤት ሲሆኑ አስተዳደር ውስጥ ይገባሉ። ስለዚህ ቴክኖሎጂውንም እውቀቱንም ይዘው ይመጣሉ። ይህ ሲሆን ደግሞ በአገር ውስጥ ያሉ ባንኮች ዕድል ይኖራቸዋል፤ ለምሳሌ እስከ 49 በመቶ ድረስ ባለቤትነት ይዘው ቢቀመጡ ከአምስት ዓመት በኋላ የእስቶክ ማርኬት (ካፒታል ማርኬት) ተቋቁሞ በሥራ ላይ እንደሚሆን ተነግሮናልና የባንኮቹ ሼር እዛ ይሸጣል። ታዲያ እነዚህ ከውጭ የገቡ ባንኮች የባንኮቹን ካፒታል የበለጠ ለመያዝ ከፈለጉ በዛ መልክ ይገዙታል። ከጊዜ በኋላ መቶ በመቶም ለመያዝ ነፃነት ይኖራል ማለት ነው። በመጀመሪያ ግን በዚህ መልክ ቢገቡ ይመረጣል ባይ ነኝ። ስለዚህ አንድ ቀን ተነስተን ከዛሬ ጀምሮ መጥታችሁ በኢትዮጵያ የባንክ ገበያ ውስጥ እንዳሻችሁ ሆኑ እንዳይባል ያስፈልጋል ሲሉ ስጋታቸውን አስረድተዋል።

ከወራት በፊት የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ፣ የኢትዮጵያ ባንኮች ሁለት አስርት ዓመታት ብቻቸውን የመሥራት ዕድል አጋጥሟቸው መቆየታቸውን አስታውሰዋል። በአሁኑ ወቅት ግን ይህንን ዕድል ማቆየት አይቻልም፤ አገሪቱ ተጨማሪ የውጭ ምንዛሪና ተጨማሪ ሀብት ስለሚያስፈልጋት የውጭ ባንኮች ወደአገር ቤት መምጣታቸው እንደማይቀር ይጠቅሳሉ። ስለሆነም የኢትዮጵያ ባንኮች አሠራራቸውን በማዘመን ራሳቸውን ለዚህ ውድድር ማዘጋጀት እንዳለባቸው አሳስበው መንግሥትም የውጭ ባንኮች ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ የፖሊሲ ማሻሻያ ለማድረግ እየተዘጋጀ መሆኑንም ማስታወቃቸው ይታወሳል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በተጠናቀቀው በጀት ዓመትም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባንኮቹ ያላቸው ሀብት እያደገ መምጣቱንና በአሁኑ ወቅትም 2 ነጥብ 3 ትሪሊዮን ብር መድረሱን ገልጸዋል። በመላ አገሪቱ ያሉት የባንክ ቅርንጫፎችም ከስምንት ሺ በላይ መድረሳቸውንና ይህም ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር በ17 በመቶ ብልጫ ማሳየቱን ተናግረዋል። ባንኮቹ በተጠናቀቀው በጀት ዓመትም 353 ቢሊዮን ብር ብድር ማቅረባቸውንም አስታውሰዋል።

በቅርቡ የአማራ ባንክ ይፋዊ የሥራ ማስጀመሪያ ሥነ ሥርዓት ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥ ዶክተር ይናገር ደሴ እንዳሉት፤ የአማራ ባንክ ወደማህበረሰቡ በመድረስና ከፍተኛ የአክሲዮን ድርሻን በመሸጥ እንዲሁም ከፍተኛ የተከፈለ ካፒታል ይዞ የባንክ ኢንዱስትሪውን በመቀላቀል ረገድ ቀዳሚ ነው። በቴክኖሎጂና በአገልግሎት አሰጣጥ ተወዳዳሪ እና ቀዳሚ መሆን እንዲችል ባንኩ ራሱን እንዲያዘጋጅም አሳስበዋል። ይህ ከአገር ውስጥ ብቻም ሳይሆን ወደ ኢትዮጵያ እንደሚገቡ ከሚታሰቡ የውጭ ባንኮች ጋር ለመወዳደር እንደሚያስችል ያስረዳሉ። እንዲገቡ ከሚጠበቁት የውጭ ባንኮች ጋር ለመወዳደር ትልቅ ዝግጅት ይጠብቀናል ሲሉ ተናግረው፤ ለዚህም የአማራ ባንክን ጨምሮ ሌሎች የኢትዮጵያ ባንኮች ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ ጥሪ ማቅረባቸው ይታወቃል።

አቶ ዛፉ ኢየሱስወርቅ እንደሚሉት፤ አሁን ባለንበት ሁኔታ ባንክ ለመክፈት ሕጉ የሚለው አምስት ቢሊዮን ብር ካፒታል ነው። በአሁኑ ወቅት ይህን ካፒታል ያላሟሉ ብዙ ባንኮች አሉ። እነዚህ አምስት ቢሊዮኑን ብር ካሟሉትም ጋር ሆነ ካላሟሉት ጋር ውህደት መፍጠር ይኖርባቸዋል። ከተቋቋሙት ባንኮች ውስጥ የውጭዎቹ ባንኮች መጥተው ይገዛሉ ከተባለም ለውጭዎቹም ይሸጣሉ፤ ነገር ግን የውጭዎቹ የሚፈቀድላቸው ለመጀመሪያ ሦስት ወይም አምስት ዓመት እስከተወሰነ መቶኛ ድረስ ስለሆነ የውጭዎቹ የሚፈቀድላቸው የተሻለ የሚሆነው አቅማቸውን እያዩ አምስት ቢሊዮን መድረስ የማያስችላቸው መስሎ የታያቸው ባንኮች ከሌሎች ባንኮች ጋር እየተወያዩ አንድ ላይ መዋሃድ ነው። ይህ አፋጣኝ የሆነ አስፈላጊው ጉዳይ ነው። ለኢትዮጵያ የባንኮች ውህደት በጣም አስፈላጊ ነው። ለውጭ ገዥዎችም ትንሽ እንኳን የሚያጓጉ ሆነው እንዲታዩ ውህደት ወሳኝ ነው። ይህ በእኔ እይታ አንድ ቁም ነገር ነው ብዬ የምወስደው ነው። ከዚህ በተረፈ በኢትዮጵያ ውስጥ ትልልቅም የሚባሉት በአሁኑ ጊዜ ምናልባት ሦስት ወይም አራት ባንኮች ቢሆኑ ነው። እነዚህም ቢሆኑ ብቻቸውን አቅማቸው በቂ አይደለም። እነርሱም ራሳቸው አገር ውስጥ ካሉ ባንኮች ጋር መዋሃድ ይጠቅማቸዋል። ከውጭዎቹም ጋር ሼራቸውን በመሸጥ ከእነርሱም ጋር መቀናጀቱ ይጠቅማል።

ውድድሩን መቋቋም ያልቻሉ ባንኮች ዕጣ ፈንታቸው ሊገዛቸው ለሚችል ባንክ መሸጥ ነው። አቅም ያላቸው ባንኮች እንዲገዟቸው ማድረግ ነው። በሌላ ቋንቋ ይዘጋሉ ማለት ነው። ሌላ አማራጭ የለም።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# ከአጭሩ ቀሚስ በስተጀርባ

**ሰላማዊት ውቤ**

‹‹ዋው ዋው! ብራቦ ! እንዲህ ዓይነቱ አለባበስ ነው የሚያስፈልገው። እየመጣ ነው ቀጣሪሽ በፍጥነት ይዞሽ ይሄድና አሁኑኑ ሥራሽን ትጀምሪያለሽ›› በአዲስ አበባ ከሚገኙ በርካታ ሥራና ሠራተኛ አገናኞች አንዱ የአስተናጋጅነት ሥራ ፈልጋ ለመጣች ወጣት ሲሰጣት የሰማሁት አድናቆት የተሞላ መልስ ነው።

አገናኙ ፍቃድ ይኑረው አይኑረው የጠየቀው ባይኖርም አምስት ኪሎ የሸዋ ዳቦ ቤት ግድግዳን ተደግፈው ከቆሙት ሥራ ፈላጊዎች አንዷ የሆነችውንና መልስ የሰጣትን ወጣት የሚያይበት አስተያየትም ልክ አልነበረም። ዓይኑ እጥረቱ የውስጥ ሱሪዋን መደበቅ እንኳን የተሳነው የሚመስለው አጭር ቀሚስ ላይ ብቻ ተተክሎ አልቀረም። ዳሌዋን፤ ባቷን እያለ እስከ እግር ጥፍሯ ወረደ። እንደ ሸቀጥም ሁሉ ከኋላዋ ዞሮ እየቃኛት ‹‹አይ መቀመጫ ሰጥቶሻል! ሲልም በአድናቆት ከማሳረጉ፤ የልጅቱ ቀጣሪ ክላክስ አደረገ። ቀጣሪውም ቢሆን ምርጫው ልጅቱ ነበረች። መኪናው ድረስ ሸኝቶ በጥድፊያ ወደ ሌሎቹ ሥራ ፈላጊዎች መለስ ያለው አገናኝ ታዲያ በየትኛውም ዓይነት ቦታና ደረጃ ላለ አስተናጋጅነት መቀጠር የሚፈልጉ የልጅቱን ዓይነት አለባበስ መከተል እንደሚገባቸው በቁም ነገር አሳሰበ። ማሳሰቢያው ትዕዛዝና ግዴታ ጭምርም ነበር።

ሆኖም የእንዲህ ዓይነቱ የአለባበስ ግዴታ ሕጋዊ መሠረት እንደሌለው ከሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ያገኘሁት መረጃ ያመለክታል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ያለውን ሀሳብ በይደር ላቆየውና ሴቶች ለአስተናጋጅነት ሙያ ለመቀጠር አጭር ቀሚስ መልበስ እንዳለባቸው የሚያስገድዱት እነማን ናቸው፤ ለምንድነው የሚያስገድዱት፤ አጭር ቀሚስ ፋሽን ነው አይደለም፤ ከሆነ አንዳንድ ወንዶች ከለከፋ ጀምሮ ሴቶች ላይ ወሲባዊ ትንኮሳ ለማድረስ ይገፋፋናል የሚሉት ለምንድነው? በሚሉት ሀሳቦች ዙሪያ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የሰጡኝን አስተያየት ላጋራችሁ።

አቶ ፋሲል ሞገስ ቦሌ መድኃኒዓለም አካባቢ የሚገኘው የቤስት ዌስተርን ፓላስ ኢንተርናሽናል ሆቴል ማኔጀር ናቸው። እንደሳቸው ባንክም ሆነ ሌሎች ተቋማት ላይ ዩኒፎርም የሚዘጋጅበት ምክንያት አላስፈላጊ የግል አለባበሶችን ለመከላከል ነው። የትኞቹም ተቋማት ላይ ከጉልበት በላይ የሆነ ልብስ መልበስ አይፈቀድም። በሙያቸው ሲሠሩ ሆቴሉ ሾስተኛቸው በመሆኑ ስለ አስተናጋጆች አለባበስ ያውቃሉ። ሴቶች እሳቸው በሠሩባቸው ሾስቱም ሆነ ሌሎች ኢንተርናሽናል ሆቴሎች በሙሉ ከፓንት ማይተናነስ አጭር ቀሚስ እንዲለብሱ አይገደዱም። የለበሰች ብትገኝ ከሥራ ትባረራለች። በቤስት ሆቴል የሚፈቀደው እስከ ጉልበት አንዳንዴም ከጉልበት አለፍ ያለ ቀሚስ ወይም ሰውነታቸው ላይ ያልተጣበቀ ሱሪ ነው። ምክንያቱም ደንበኞች በአለባበሳቸው ተስበው በሴቶቹ ላይ ሌላ ፍላጎት እንዲያሳድሩ አይፈለግም።

አቶ ፋሲል እንደታዘቡት ባርና ሆቴል ላይ የሚሠሩ ሴት ወጣቶች ወድደው ሳይሆን ተገድደው ነው አጭር ቀሚስ የሚለብሱት። ተግባሩ እስከ ታች ሥጋ ቤትና ትናንሽ ምግብ ቤቶች እየተለመደ መጥቷል። ካለዚያ ሥራውን አትሠሪም ይባላሉ። አሠሪዎቻቸው እንዲለብሱ የሚያስገድዷቸው እነሱን እያለ ገበያ እንዲመጣላቸው ነው። ከዚህ ባሻገር ወደ ዝሙትም እንዲገቡ ይገፋፋል። መገደዳቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ቀሚሱ በተለይ ቡና ቤት ውስጥ የበለጠ ለጥቃትም ያጋልጣቸዋል። ሆኖም እንዲለብሱ ያስገደዷቸው አሠሪዎቻቸው ጥቃቱን እንኳን አይከላከሉላቸውም።

እነሱ ሆቴል ከልብስ ጋር ተያይዞም ባይሆን በስካር መንፈስም ሆነ በሌላ ተነሳስቶ ሴት አስተናጋጆችን የተነኮሰ ለእንግድነቱ ከሚሰጠው ክብር ባሻገር በሕግ ያስጠይቀዋል። በመስተንግዶ ሥራ ከተሠማሩት ውጪ ያሉ ሴቶች አጭር ቀሚስ መልበሳቸው ክፋት የለውም። አጭር ቀሚስ አደረገች ብሎም መናገሩም አግባብ ነው ብዬ አላምንም። ሆኖም አንዳንድ ሰዎች ስሜታዊ ሲሆኑ ስለማይ ባትለብስ እመክራለሁ ይላሉም አቶ ፋሲል።

ወጣት አልማዝ ሳህሌ በዚህ ሆቴል ውስጥ ተቆጣጣሪ ነች። ከላየን ኢትዮጵያ ኮሌጅ በሆቴል ማኔጅመንት ለአራት ዓመታት የዲግሪ ትምህርቷን ተከታትላ ከተመረቀች በኋላ ካፒታል፤ ፍሬንድ ሽፕና እንቢልታ ሆቴልን ጨምሮ በተለያዩ ሆቴሎች ለአምስት ዓመታት በአስተናጋጅነት ሠርታለች። እሷን ጨምሮ በሆቴሉ የሚሠሩ ሴት አስተናጋጆች ከጉልበት አለፍ ያለ ቀሚስን ጨምሮ ሱሪ፤ ኮትና ሸሚዝ ዩኒፎርም ነው የሚለብሱት። ነገር ግን እንደታዘበችው በምሽትና በተለያዩ ቦታዎች እንዲህ ዓይነቱን አጭር ቀሚስ ካለበሳችሁ የሥራ ዕድሉን አታገኙም የተባሉ ወጣት ሴቶች ታውቃለች። ኑሯቸውን ለማሸነፍ ሲሉ እንቢ አይሉም። ሥራውን ማግኘት ግድ ስለሚላቸው ይለብሳሉ። ነገር ግን አንዳንድ ወንዶች ቀሚሱን የለበሱ ሴቶችን የመተናኮልና የማይሆን ነገር ውስጥ የማስገባት ባህርይ አላቸው። ስለዚህ ከሆቴሉ ሠራተኛ ይልቅ የሆቴል ባለቤቶች ለሴት አስተናጋጆች ለጥቃት የማያጋልጥ ዩኒፎርም ማዘጋጀት አለባቸው ትላለች።

‹‹ወድጄ ነው! ወደሽ ከተደፋሽ ቢረግጡሽ አይክፋሽ አለች አያቴ›› ያለችኝ ደግሞ አጭሩን ቀሚስ ለምን እንደለበሰችና ያም ይሄም የሚጎትታት በቀሚሱ ምክንያት መሆኑንና አለመሆኑን እንድትነግረኝ የጠየቅኳት ወጣት ናት። እንደ አሸን ከፈሉት የከተማችን ሥጋ ቤቶች በአንዱ ያገኘኋት ስሟን ልትነግረን ፈቃደኛ ያልሆነችው ወጣቷ አስተናጋጅ እንዳጫወተችኝ የ12ኛ ክፍል ትምህርት ብታጠናቅቅም ውጤት ስላልመጣላት ሁለት ዓመት ያለ ሥራ ተቀምጣለች። በዚህ መካከል ብታገባምና ሁለት ልጆች ብትወልድም ባሏ ሥራ አልነበረውም። ከዚህ በኋላ በወላጅ እርዳታ የመስተንግዶ ትምህርት ተማረች። እዚህ ሥጋ ቤት ከፓንት የማይተናነሰውን ልብስ መልበስ ግዴታ እንደሆነ በአስቀጣሪዋ ደላላ አማካኝነት ሲነገራት አቅማምታ የነበረ ቢሆንም አማራጭ በማጣቷ ተቀጠረች።

ከሥራ ዩኒፎርም ውጪ ሌላ ዓላማ ይኖረዋልም ብላ አላሰበችም። ሥጋ ቤቱ ውስጥ ድራፍትንና ቢራን ጨምሮ የተለያዩ የአልኮል መጠጦችም ይሸጣሉ። የሥጋ ቤቱ ደንበኞች በዚህ የተነሳ ለመስተንግዶ ስታልፍ ስታገድም ይጎነትሏታል። ከዚህም አልፎ አንሶላ ለመጋፈፍ የሚጠይቋት ብዙ ናቸው። እንደገባች ሰሞን ትሳደብና ትናደድ ነበር። ሴት አዳሪ ሳልሆን አስተናጋጅ ነኝ እላቸው ነበር ስትልም ታስታውሳለች። ሆኖም ባለቤቱ ለደንበኞቼ እንዲህ ዓይነት ምላሽ አትመልሺ፤ ገበያየን ታርቂብኛለሽ እያለ በተደጋጋሚ ያስጠነቅቃት እንደነበርም ታወሳለች። አማራጭ በማጣቷ እየለመደችው መጣች።ሥራ ያልነበረው ባሏ ሥራውን መሥራቷን በመቃወሙ ጥሏት ጠፍቷል። ሳታስበው የዝሙት ሥራ ውስጥ ብትገባም ለዝቅተኛ የወር ደመወዟ መደጎሚያ ሆኗታል።

አኒሳ አብዲ ትባላለች። ድሬዳዋ ብዙኃን መገናኛ ኤፍኤም ድሬ 106 ነጥብ 1 በሴቶች ብቃትና ፖለቲካዊ ተሳትፎ ላይ ትኩረት ያደረገ ብቁ ሴት የተሰኘና በአማርኛ ቋንቋ የሚተላለፍ የሬዲዮ ፕሮግራም አዘጋጅ ነች። በኦሮሚያ ቋንቋ በሚተላለፈው የቴሌቪዥን ፕሮግራምም መዝናኛ ፕሮግራም አዘጋጅ ሆና እየሠራች ትገኛለች። አለባበስ እንደየ ግለሰቡ ምርጫ የሚወሰን መብት ነው የሚል አቋም አላት። ነገር ግን አጭር ቀሚስ ከባህላዊና ሃይማኖታዊ አለባበስ ጋር አይመደብም። ከውጭ የመጣና ከጊዜ ብዛት የራሳችን አድርገን የተቀበልነው ፋሽን ነው ትላለች።

ሆኖም አንዳንድ ወንዶች ራሱ ኅብረተሰቡም በብዛት ለሴቷ ከራስ እስከ ጥፍሯ ትሸፋፈን በሚል ሕግ አጥረውና ድንበር ሠርተውላታል። ሆኖም ይሄ የሴቷን መብት መጋፋት ነው። የአመለካከትና ራስን ለመቆጣጠር ያለመቻል የወንዶቹ ችግር ነው። አኒሳ ወጣት ሴቶች ይሄን ፋሽን በመከተላቸው ከለከፋ ጀምሮ ለወሲባዊ ጥቃት ይጋለጣሉ በሚለው አትስማማም። አንዲት ሴት እንደ ዘመናዊ



ሴት አጭር ቀሚስ ልትለብስና ፋሽኑን ልትከተል ትችላለች። ይሄም መብቷ ነው ባይ ናት።

ከስድስት ወር ጨቅላ ሕፃናት ጀምሮ አረጋውያን፤ አካል ጉዳተኛ፤ በተለያየ ዕድሜ ደረጃ ያሉ ሴቶች የተደፈሩትና በወንዶች እየተለከፉ ያሉት አጭር ቀሚስ አድርገው ነው ወይ? ስትልም ትጠይቃለች። አጭር ቀሚስ ስላደረጉ አይደለም እየተደፈሩና ጥቃት እየደረሰባቸው ያሉትም ትላለች። ለለከፋና ለተለያዩ ወሲባዊ ጥቃቶች ስለሚያጋልጣት አትልበስ የሚለውንም የኅብረተሰቡ የአመለካከትና ራስን ለመቆጣጠር ያለመቻል የወንዶቹ ችግር ነው ባይ ነች። ይሄን ለመለወጥ ኮቪድ 19 በተስፋፋበት ሰሞን ሴቶች ላይ እንደደረሰው የቤት ውስጥ ጥቃት የአንድ ሰሞን ዘመቻ ብቻ ሳይሆን ተከታታይ ሥራ እንደሚያስፈልግም ትመክራለች። በዚህ በኩል እሷ በብቁ ሴት የሬዲዮ ፕሮግራሟ ተግታ እንደምትሠራም ታወሳለች። አሁን ያለውን ትውልድ ማትረፍ የተቻለው ተከታታይነት ባለው መልኩ በኤች አይቪ ኤድስ ላይ በመሠራቱ መሆኑን ታነሳለች።

በአዲስ ዘይቤ ዲጂታል ጋዜጣ የሚሠራው ወጣት ኢያሱ ዘካርያስ አንዲት ሴት የፈለገችውን የመልበስ መብት አላት ይላል። ራሷን ዝቅ ታድርግ የሚል ዕምነት የለኝም። በተለይ ወጣት ሴት ዕድሜ ደረጃዋ የሚፈቅደውን ፋሽን ሁሉ መከተል እንዳለባት እንደሚያምንም ያወሳል። ሆኖም በለበሰችው አጭር ቀሚስ ምክንያት ከወንዶች ከለከፋ ጀምሮ የተለያዩ ጾታዊ ትንኮሳዎች እንዲሁም ከኅብረተሰቡ መገለል ሲደርስባት አስተውሏል። ለወሲብ አነሳሳኝ የሚሉ ወንዶችም ገጥመውታል። እነዚህ ሰዎች እርቃን መሄድ ባህላቸው የሆነ ሴቶች አካባቢ ቢሄዱ ምን ሊሉ ነው? ሲልም ይጠይቃል። የባህርይንና የአመለካከት ችግርን እንዲሁም ሃይማኖትን ከፋሽንና መብት ጋር ለያይተው ማየት እንደሚገባቸው ይመክራል። በበኩሉ በምንም ያህል መጠን የሚለበስን አጭር ቀሚስ ከፋሽን ጋር ብቻ እንደሚያያይዘው ያወሳል።

ስሟ እንዲገለፅ ባትፈልግም የነቃች የበቃች የምትባል ዓይነት ሴት ናት። በምትሠራበት በኦን ላይን ሚዲያ አብዝታ ትታወቅና ትደነቃለች። እንደነገረችን አጭር ቀሚስ ለባሽ ነች። የምትለብሰው በፋሽን መልኩ ነው። ሁሉም ቀሚሶቿ ከጉልበቷ በላይ ናቸው። ፈልጋ ወድዳና ፈቅዳ እንዲሁም ለራሷ በሚመቻት መልኩ ነው የምትለብሰው። ቀሚሱን የምትገዛውም ራሷ ናት። ሁሉም ቀሚሶቿ ከጉልበቷ በላይ ናቸው። አጭር የምትለብሳቸው ለራሷ በሚመቻትና ምቾት በሚሰጣት መልኩ ነው። ሆኖም አጭር መልበሷ ለማንኛውም ጾታዊ ትንኮሳም ሆነ ለመደፈር ያጋልጠኛል የሚል ዕምነት የላትም። እንዲህ እንደ እሷ ያለ ቀሚስ የለበሰችን ሴት ልጅ ለክፈው ወይም ጾታዊ ትንኮሳ አድርሰው አጭር ቀሚስንም ሆነ ሌላ አለባበስን ምክንያት የሚያደርጉ ወንዶችን እንዲሁም አለባበስን ችግር የሚያደርጉ የኅብረተሰብ ክፍሎችን አጥብቃ ትቃወማለች።

‹‹ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ወንዶችም ጋር ብዙ የአለባበስ ችግሮች አሉ›› የምትለው ወጣቷ ወንዶች ፋሽን ነው ብለው የውስጥ ሱሪያቸውን ዝቅ አድርገው እያሳዩ ይሄዱበታል። ሲክኒ ሱሪ ለብሰውና ደረታቸውን ገልብጠው ሲሄዱ እኛ ስሜታችንን ያነሳሳል አላልንም ትላለች። በመሆኑም ችግሩ አጭር መልበስ ሳይሆን የወንዶቹና የኅብረተሰቡ የአስተሳሰብ ችግር እንደሆነ ታሰምርበታለች።

እኔ አጭር ቀሚስ መልበስን በፈቃደኝነትና ከፍቃድ ውጪ በሁለት ከፍዬ አየዋለሁ የምትለው ወጣቷ በዚህ በኩል ግን ጥንቃቄ ሊወሰድ እንደሚገባ ትጠቅሳለች። ሰሞኑን በማህበራዊ ሚዲያ ሲያነጋግር የቆየውን አዲስ አበባ ከተማ ላይ የሚገኙ አብዛኞቹ ሥጋ ቤቶች አስገድደው እያስለበሷቸው ያሉ የእንስት አስተናጋጆች ጉዳይም ታነሳለች። ‹‹ሰውየው ከቤቱ ኪሱን እንጂ የልጅቱን ገላ አስቦ አይወጣም›› የምትለው ወጣቷ ድርጊታቸው የሴቷን መብት ያልጠበቀ፤ ለብርድና ቁርጥማት የሚያጋልጥ የግለሰቦችን ጥቅም የሚያስጠብቅ ከመሆኑም ባሻገር በእንስቶቹ፤ በቤተሰባቸውና በአገሪቱም ላይ ዝሙትን በማስፋፋት ታላቅ ማህበራዊ ቀውስ እንደሚያስከትልም ታስጠነቅቃለች።

ሴቷ ጭኗ ስለታየ የበለጠ ይበሉና ይጠጣሉ በሚል ሴት ወጣቶችን በመጠጥ በተሳከረ ሰው መኻል ተጋላጭ የማድረግ አለባበስ እንደ ፋሽን ወስዶ ዝም ማለት እንደማይገባና ቁርጠኛ እርምጃ እንደሚፈልግም ታሳስባለች። ሆኖም ይሄም ችግር አሁንም የሥራ አማራጭ ስላጡ የገቡበት እንስቶች ሳይሆን የአሠሪዎቻቸውና በመጠጥ በመሳከር ጥቃት የሚያደርሱ ወንዶች እንደሆነም ታወሳለች።

ትርሲት አሰፋ በአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን ቴሌቪዥን ዝግጅት የትምህርታዊ ፕሮግራም አርታኢ ነች። የእንስቷን አጭር ቀሚስ መልበስ አትደግፍም። ፋሽንነቱንም አታበረታታም። ሴቶች አጭር ቀሚስ ለብሰው ሳይ ራሳቸውን እንደ ጣሉ እቆጥራለሁ። ምክንያቱም ከጉልበቷ በላይ ልብስ ለበሰች ማለት ግማሽ ድረስ ያለው አካሏ እርቃን ሆነና ለትንኮሳ ራሷን አጋለጠች ማለት ነው። ክብሯንም ያዋርዳል። ወንዶችንም ያሰናክላል ትላለች።

የኢትዮጵያ አየር መንገድን ጨምሮ፤ ባንኮችና ትልልቅ የሚባሉት ዓለም አቀፍ ተቋማት ይሄን ልብስ እያበረታቱና እየደገፉ አስገዳጅ እያደረጉት ነው። ከዚህ ተነስቶም ልብሱ እስከ መንደር ምግብ ቤቶች እየተለመደ መጥቷል።በአስተናጋጅነት ሥራ ለመቀጠርም እንደ አንድ አስገዳጅ የቅጥር መስፈርት እየተወሰደ ነው የሚሉ እሳቤዎች በአንዳንድ ኅብረተሰብ ክፍሎች መደመጡን የምትናገረው አርታይዋ ጉዳዩ በተጨባጭ በአስተናጋጆቹ ላይ ተፅዕኖ የመፍጠሩ ዕውነታ በጥናት የሚመለስና ማጣራትን የሚፈልግ እንደሆነም ታወሳለች።

ከአጭር ቀሚስ ጋር በተያያዘም ሴቷ እስከ ባቷ ድረስ ለብሳ እየጨነቃትና ጉርዷን አስሬ ወደ ታች ዝቅ እያደረገች ስታስተናግድ ገጥሟታል። ወንዱ በፊናው ከነ ክርባቱ ሱሪና ኮቱን ገጭ አድርጎ ዘና ብሎ ሲያስተናግድ እሷ ብርድ የወለደው ቁርጥማት እግሯን እያነካት ፊቷን ቅጭም አድርጋም ታዝባለች። ካልተመቸሽ ለምንድነው የለበሽው ስትላት የእንጀራ ጉዳይ ነው የሚል ምላሽ እንደሰጠቻትና ከዚህ ተነስታ ልብሱን እንስቶቹ በባለቤቶቹ ተገደው እንደለበሱ ለመረዳት መቻሏን ታወሳለች። አጭር ቀሚስ ካለበሰች ማስተናገድና ሕይወቷን መምራት ያለመቻሏ ጉዳይ አሳሳቢና እንደ ሴት ሴቶች ድምፃቸውን ሊያሰሙበት የሚገባ ጉዳይ መሆኑንም ትጠቁማለች። ትርሲት የድሮዎቹን የእናቶች ግርማ ሞገስ ያላቸውና እስከ ጉልበት የደረሱ ሚኒስካርት የተሰፉ አጭር ቀሚሶችእንደምትደግፍም አጫውታኝ ሀሳቧን አሳርጋለች። ለመሆኑ ሴቶች ሥራ ለመቀጠር ሲሉ አጭር ቀሚስ እንዲለበሱ የሚያስገድዱ አሠሪዎችን በተመለከተ ሕጉ ምን ይላል? ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከተው የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርስ ጉዳዩን እንደምን ይመለከተዋል የሚለውን ሳምንት እንመለስበታለን፡፡

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

የክረምቱ ወቅት እንደ ቀጠለ ነው፡፡ ታዲያ በዚህ ወቅት ከሚጥለው ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ የተለያዩ አደጋዎች በተለያዩ አካባቢዎች ሲከሰቱ ማየት የተለመደ ነው፡፡ ሰሞኑንም በጣለው ከባድ ዝናብ የተነሳ በመዲናችን አዲስ አበባ ሳይቀር የተለያዩ በአንዳንድ አካባቢዎች መከሰታቸውን ከተለያዩ የዜና ምንጮች ተረድተናል፡ ፡ በክረምት ወቅት ይህ የተለመደ ነው፡፡ ከግምሽ ምዕተ ዓመት በፊት በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች በክረምት ወቅት የሚከሰቱ ችግሮችና አደጋዎች ምን ይመስሉ እንደነበረ በዛሬው የአዲስ ዘመን ድሮ አምዳችን መለስ ብለን ለመቃኘት ሞክረናል፡፡ በወቅቱ ይሠሩ የነበሩ የልማት ሥራዎች በክረምቱና በዝናብ ምክንያት በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች የደረሰባቸውን አደጋዎችን በሚመለከት የተሰሩ ዘገባዎችንም መርጠን አቅርበናል፡፡

### ዝናብ በሕይወትና በንብረት ላይ ጉዳት አደረሰ

ደብረ ማርቆስ ደብረ ብርሃን አሰላ ደሴ (ኢ-ዜ-አ-)፤በጐጃም በሸዋ በአሩሲና በወሎ ጠቅላይ ግዛቶች በሚገኙት አንዳንድ ቀበሌዎች ሰሞኑን ዝናብ አስከትሎ የወረደው መብረቅና የተነሳው ኃይለኛ ነፋስ በሕይወትና በንብረት ላይ ጉዳት አደረሰ፡፡

በጐጃም ጠቅላይ ግዛት በቆላ ደጋ ዳሞት አውራጃ በደንበጫ ወረዳ ደብሪት ቀበሌ ከዘነበው ዝናብ ጋር የወረደው መብረቅ ፩ ሰው ገድሎ ሌሎች ፪ ሰዎች አቁሱሏል፡፡ በሸዋ ጠቅላይ ግዛት በመንዝና ግሼ አውራጃ ባለፈው ሳምንት ከዝናብ ጋር የነፈሰው ኃይለኛ ነፋስ የ፵፫ ሰዎች መኖሪያ የነበሩትን ፩፻፩ ክፍሎች የቆርቆሮ ክዳን ቤቶች አፈራርሶ ከአገልግሎት ውጪ አድርጓል፡፡

በአሩሲ ጠቅላይ ግዛት በገደብ ወረዳ በአሳሳ ከተማ ላይ በዚህ ሳምንት በተነሳው ኃይለኛ ነፋስ ፭ ክፍል ቤቶች መፈራረሳቸው ተረጋግጧል፡፡ በወሎ ጠቅላይ ግዛት በወረኢሉ አውራጃ በካቤ ከተማ ባለፈው ሳምንት የነፈሰው ኃይለኛ ነፋስ ስድስት የቆርቆሮ ክዳን ቤቶች አፈራረሰ፡፡ በዚሁ ኃይለኛ ነፋስ ምክንያት የፈራረሱት ክፍሎች ፬ የመኖሪያ ቤቶች ክፍሎች ናቸው፡ ፡ የአውራጃው ግዛት ዋና ጸሐፊ አቶ አሰፋ መኩት እንደገለጡት፤በዚሁ የነፋስ አደጋ በሰውና በእንስሳት ላይ የደረሰ ጉዳት የለም፡፡

(ሰኔ 17 ቀን 1964 ዓ.ም የወጣው አዲስ ዘመን)

### በአረጐ ተራራ ላይ 500ሺህ የዛፍ ችግኞች ለመትከል ዝግጅት በመደረግ ላይ ነው

ደሴ (ኢ-ዜ-አ-) ከደሴ ከተማ ፲፪ ኪሎ ሜትር ርቆ በሚገኘው የአረጐ ተራራ ላይ በመጪው ክረምት ፭፻ሺህ የዛፍ ችግኝ ለመትከል የሚያስችል ሥፍራ ለተከላው የሚያመች ሥፍራ በመዘጋጀት ላይ ይገኛል፡፡

የአረጐ ተራራ የደን ጫካ ለማድረግ በተወሰደው ርምጃ መሠረት፤አፈሩ በጐርፍ ውሀ እንዳይወሰድ በሚከለክል መንገድ ለችግኞች ተከላ በሚያመች አኳኋን ሥራው የተጀመረው ባለፈው የካቲት ፳፬ ዓ/ም ሲሆን፤ይህም ሥራ በጥቂት ቀኖች ውስጥ እንደሚጠናቀቅ ይጠበቃል፡፡

በመደብ እየተከፈለ በዘመናዊ ዕቅድ በተዋረድ በመዘጋጀት ላይ የሚገኘው የዚህ ችግኝ መትከያ ሥፍራ ሥራ የሚካሄደው በአሜሪካ ምግብ ለሥራ ፕሮግራም ክፍልና የዓለም ምግብ ድርጅት ኅብረት መሆኑን የሥራው አላፊ አቶ ወልደኪዳን ንርኤ ፤ክቡር ደጃዝማች ሰሎሞን አብርሃም የወሎ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ ባለፈው ሳምንት የሥራውን ይዞታ በተመለከቱበት ወቅት ገልጠዋል፡፡

በአረጐ ተራራ ላይ እስካሁን ድረስ ከ፬፻፶ ኪሎ ሜትር በላይ፤ርዝመት ያለው ሥፍራ ለዛፍ ተከላ ሥራ በሚያመች ሁኔታ ተዘጋጅቷል፡፡ ይህንንም ተግባር ለሚያከናውነው ሰው በቀን ፫ ኪሎ ስንዴ ይሰጠዋል፡፡ በዚህም መሠረት ካለፈው የካቲት ወር እስከ ግንቦት ፲፪ ቀን ፳፬ ድረስ ፭ ሺህ ፬፻፺ ሰዎች የሥራው ተካፋዮች በመሆን ፤፩ሺህ ፭፻፳፪ ኪሎ ስንዴ ተቀብለዋል፡፡የዚህም አሠራር ዘዴ ዓላማ ፤ሥራን በመፍጠር ለሠራተኛው ሕዝብ ተመጣጣኝ የአገልግሎት ዋጋ እየከፈሉ አስፈላጊ በሆኑ ሥፍራዎች ላይ ዛፎች በብዛት እንዲተከሉ ለማድረግ መሆኑን አቶ ወልደኪዳን አስረድተዋል፡፡

በዚሁ የምግብ ለሥራ ፕሮግራም ወደፊት ለሚተከሉ ዛፎች ሥራ አመቺ እንዲሆን ተራራውን የሚያስወጣ ፪ ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው ጊዚያዊ የመኪና መንገድም ተሠርቶ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል፡፡

ክቡር ደጃዝማች ሰሎሞን አብርሃም በጉብኝቱ መጨረሻ ፤ፕሮግራሙ እጅግ ጠቃሚ መሆኑን ጠቅሰው፤ሥራውን ፈጥሮ ሕዝቡ እንዲጠቀም መደረጉም በሕዝቡም ዘንድ የዛፍ ተከላን ሥራና ጥቅም በይበልጥ ለማሳወቅ እንደሚረዳ ያላቸውን እምነት ገልጠዋል፡፡

ከደሴ ከተማ ኮምቦልቻ በሚወስደው መንገድ ፲፪ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሚገኘው አረጐ ተራራ ባለፉት ሁለት ዓመቶች ውስጥ ላይ ከ፫፻ ሺህ ባላይ የዛፍ ችግኞችን የወሎ ጠቅላይ ግዛት እርሻ ጽ/ቤት ማስተከሉ ተረጋግጧል፡፡

(ግንቦት 23 ቀን 1964 የወጣው አዲስ ዘመን)

### በሮቢት የሚገኙ እሥረኞች 40 ጋሻ መሬት በማልማት ላይ ናቸው

በሮቢት ፳፫ ጋሻ መሬት በተጨማሪ ለሥራ እንዲውል ተፈቅዶ የወኅኒ ቤቶች ጽ/ቤት መረከቡን አቶ አሰፋ መርጊያ በሰጡት ወሬ ለማወቅ ተችሏል፡፡ይህም ማለት ከቀድሞው ፲፯ ጋሻ መሬት ጋር ተደምሮ በሕግ እሥረኞች የሚለማው መሬት ፵ ጋሻ መሆኑ ነው፡፡ከቀድሞው ፲፯ ጋሻ መሬት ውስጥ ፲፪ቱ ለሰብልና ለፍራፍሬ አገልግሎት ሲውል አምስቱ ጋሻ መሬት ግን ለመኖሪያ ቤቶች መደልደሉን ወሬው ያስረዳል፡፡

፳፫ ጋሻ መሬት ፤ለሦስት ዓይነት ጥቅም እንደሚውል ተገልጧል፡፡ ፩ኛ ለእሥረኞች ጥቅም የሚሰጥ ሰብል መዝሪያ

፪ኛ ለፍራፍሬ ፫ኛ ለሁለቱም ማለትም ለፍራፍሬና ለሰብልዎቹ ያልሆነውን ቃጫ በመትከል ጥቅም እንዲሰጥ ተወስኗል፡፡በ፲፪ ጋሻ መሬት ላይ ይበቅል የነበረው ጤፍ ፤ማሽላ በቆሎ ፤ሰሊጥ፤አደንጓሬና ለውዝ ነው፡፡ቃጫም ለሙከራ ተተክሎ ጥሩ ውጤት መስጠቱ አቶ አሰፋ ገልጠዋል፡፡

ከዚሁ የተገኘው ሰብል በጨረታ እየተሸጠ ገቢ ይሆናል፡፡ ለዚሁ መሬት ማሚያ የወህኒ ቤቶች ጽህፈት ቤት 76.909.04 ተበድሮ ካፒታል በማድረግ ሥራው ፲፱፻፶፪ ዓ.ም ጀመረ፡፡ይህ የእርሻ ቦታ በሰው ጉልበት ብቻ ሳይከናወን ገቢ የሆነው ለውዝ (ኦቾሎኒ) 37, 101 ኪሎ፤ ጥጥ 40,992 ኪሎ፤በርበሬ 434 ኪሎ፤ሽምብራ 1,937 ኪሎ ጤፍ 21,157 ኪሎ፤ በቆሎ132,570 ኪሎ መሆኑ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በሮቢት የዶሮ ርቢ ለሙከራ ተቋቁሞ ጥሩ ውጤት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ከላይ እንደተጠቀሰው ዕዳ 180,000 ተከፍሏል፡፡በዚህ ዓይነት መሥሪያ ቤቱ በቅርቡ ያለበትን ዕዳ ሳይከፍል እንደማይቀር ይነገራል፡፡በልዩ ልዩ ሥራዎች ማለትም በጋራዥ ለመኖሪያ ቤት ሥራ ፤በግንብና በእርሻው የተሠማሩት የሕግ እሥረኞች ብዛት 500 መሆናቸውን የወህኒ ቤቶች ጽህፈት ቤት የሶሻልና ኢንዱስትሪ አማካሪ አስረድተዋል፡፡

(ጥቅምት 17 ቀን 1957 ዓ.ም ከወጣው አዲስ ዘመን)

# ዓለም አቀፍ




### የዩክሬንን እህል የጫነች የመጀመሪያዋ መርከብ ከኦዴሳ ወደብ ወደ ሊባኖስ አመራች

የዩክሬንን እህል የጫነች የመጀመሪያዋ መርከብ ከኦዴሳ ወደብ ተነሥታ ወደ ሊባኖስ ማምራቷን የቱርክ መከላከያ ሚኒስቴር ገለጸ።

ዩክሬን የእህል ምርቶቿን ወደ ሌሎች ሀገራት መላክ የሚያስችላትን ስምምነት ከሩሲያ ጋር መፈራረሟ የሚታወስ ነው። ስምምነቱን ያሳለጡት ደግሞ ቱርክ እና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ናቸው።

በዚሁ ስምምነት መሠረት በሩሲያ እና በዩክሬን መካከል ጦርነት ከተጀመረ ከ6 ወራት በኋላ እህል የጫነች የመጀመሪያዋ መርከብ ከኦዴሳ ወደብ ተነሥታ ወደ ሊባኖስ ማምራቷን ቲአርቲ የቱርክ መከላከያ ሚኒስቴርን ጠቅሶ ዘግቧል። መርከቧ 26 ሺህ ቶን በቆሎ ጭና መንቀሳቀሷም ነው የተሰማው።

እንደ አልጀዚራ ዘገባ ደግሞ ራዞኒ የተባለች የሴራሊዮን ዕቃ ጫኝ መርከብ ከ26 ሺህ ቶን በላይ በቆሎ ጭና ከኦዴሳ ወደብ ወደ ሊባኖስ አምርታለች።በአንደኛው ዙር ደረቅ ጭነት የያዙ 16 መርከቦች እንደሚነሱና ከሁለት ቀናት በሁዋላ ቱርክ እንደሚደርሱም ነው የተገለፀው፡፡

በኢስታንቡል መሰረቱን ያደረገው የጋራ ትብብር ማዕከልም የመርከቦቹን ጉዞ በሳተላይት እንደሚከታተል ተገልጿል፡፡

በጦርነቱ ምክንያት በጥቁር ባህር በኩል ለዩክሬን የግብርና ምርቶች ዝግ የነበረውን መንገድ ለመክፈት እኤአ ሐምሌ 22 ስምምነት ላይ መደረሱን አርቲ በዘገባው አስታውሷል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በተመሳሳይ ቀን ሩስያ የግብርና እና ማዳበሪያ ምርቶችን ለውጪ ሀገር ገበያ እንዳታቀርብ የተጣለውን ማዕቀብ ለማንሳት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እና ሩስያ የመግባቢያ ስምምነት መፈረሙ ተሰምቷል፡፡

የእህል ወጪ ንግዱ በሥምምነቱ መሠረት ዳግም መጀመር የዓለም አቀፉን የምግብ እጥረት ያቃልላል የምግብ ዋጋም እንዲቀንስ ያደርጋል ተብሎ ተሥፋ ተጥሎበታል፡፡



### በማዳጋስካር 32 ሰዎችን አቃጥሎ የገደለው ቡድን እየታደነ ነው

በአፍሪካዊቷ አገር ማዳጋስካር 32 ሰዎችን በቤት ውስጥ አጉረው ያቃጣሉ ግለሰቦችን የያዘ የወንጀለኞች ቡድን ለመያዝ የመንግሥት የጦር ሄሊኮፕተሮች ተሰማሩ።ፖሊስ እንዳስታወቀው የወንጀለኛ ቡድን አባላቱ በርካታ ሰዎችን የሳር ክዳን ወዳላቸው ቤቶች ውስጥ በኃይል እንዲገቡ ካደረጉ በኋላ እሳት ለኩሰውባቸዋል።

ከዋና ከተማዋ አንታናናሪቮ በስተሰሜን በምትገኘው አንካዞቤ ግዛት ውስጥ በተፈጸመው በዚሁ ጥቃት ሰለባ ከሆኑት መካከል ሴቶች እና ህጻናት ይገኙበታል።የማዳጋስካር የመከላከያ ሚኒስትሩ ለጥቃቱ በአካባቢው “ዳሃሎ” እየተባሉ የሚታወቁትን የከብት ዘራፊዎች ተጠያቂ አድርገዋል።

ከጥቃቱ በኋላ አካባቢውን የጎበኙት የመከላከያ ሚኒስትሩ ከዚህ ቀደም የፀጥታ ኃይሎች በወንበዴዎች ላይ ባደረጉት ዘመቻ ሕብረተሰቡ ለኃላፊዎች መረጃ ሰጥተዋል በሚል ኢላማ ተደርጓዋል ብለው እንደሚጠረጥሩ ተናግረዋል።

ጄኔራል ሪቻርድ ራኮቶኒሪና “ይህንን ወንጀል የፈጸሙትን እና ተባባሪዎቻቸውን አሳደን እንይዛቸዋለን’ሲሉ ተናግረዋል።በአካባቢው እየተንሰራፋ የመጣውን የከብት ስርቆት ለማስቆም እየተደረገ ያለው ጥረት ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እጅግ በጣም ጭካኔ የተሞላባቸውን ግጭቶችን አስከትሏል።

የጥቃቱ አዲስ ሰለባ በሆነችው መንደር የተቃጠሉት ቤቶች የሚያሳዩ ምስሎች በስፋት ተሰራጭተዋል።የመንግሥት ባለሥልጣናት ከጥቃቱ ተርፈው በሕክምና ተቋማት በጽኑ ሕሙማን ክፍል ውስጥ ክትትል የሚያገኙ ሦስት ሰዎችን መጎብኘታቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

# ስፖርት



# ከ20 ዓመት በታች የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ትናንት ተጀምሯል

**ብርሃን ፈይሳ**

በርካታ አስደሳች እና ታሪካዊ ትዕይንቶች የተስተዋሉበት የኦሪጎን የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ተጠናቆ ለሌላኛው የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ቦታውን ለቋል። ትናንት የተጀመረው የዓለም ከ20 ዓመት በታች አትሌቲክስ ቻምፒዮና ደግሞ ተረኛው የአትሌቲክስ ቤተሰቡ የትኩረት ማዕከል ሆኖ ለጥቂት ቀናት ይቆያል። ቀጣይ የኦሊምፒክና የዓለም ቻምፒዮና ጀግኖች የሚታዩበትና ወጣት አትሌቶች ከዓለም አቀፍ የአትሌቲክስ ወዳጆች ጋር የሚተዋወቁበት ይህ ውድድር በኮሎሚቢያዋ ከተማ ካሊ አስተናጋጅነትም ይካሄዳል።

በዚህ ቻምፒዮና ላይም ከ145 ሃገራት የተወጣጡ 1ሺ500 ወጣት አትሌቶች ተካፋይ እንደሚሆኑ የዓለም አትሌቲክስ መረጃ ያሳያል። ኢትዮጵያም በዚህ ውድድር ተካፋ ከሚሆኑ ሃገራት መካከል አንዷ ስትሆን፤ በመድረኩ 117 ሜዳሊያዎችን በመሰብሰብ በታሪክ ከዓለም አራተኛ ደረጃ ላይ ተቀምጣለች። የበርካታ ወጣት አትሌቶች ምንጭ የሆነችው ኢትዮጵያ ባለፈው ዓመት በኬንያ አስተናጋጅነት በተደረገው በዚህ ውድድር ላይ 12 ሜዳሊያዎችን በመሰብሰብ ሁለተኛ ብትሆንም በወርቅ ሜዳሊያዎች ተበልጣ በደረጃ ሰንጠረዡ አራተኛ ደረጃ ላይ መገኘቷ የሚታወስ ነው።

ዛሬ ሁለተኛ ቀኑን በያዘው በዚህ ውድድር ደግሞ 10 ሴቶችና 9 ወንዶች በጠቅላላው 19 አትሌቶችን ከ800 ሜትር እስከ 5ሺ ሜትር ባሉት ርቀቶች ኢትዮጵያን ወክለው ይወዳደራሉ። ኢትዮጵያን የሚወክለው ልኡክ በሁለት ዙር ተከፋፍሎ ወደ ስፍራው ማቅናቱ ይታወሳል። ትናንት ምሽት የወንዶች 1ሺ500 ሜትር፣ ሴቶች 800 እና 3ሺሜትር ማጣሪያ ውድድር የተደረገ ሲሆን፤ ሌሊት ላይ ደግሞ የሴቶች 3ሺ ሜትር እንዲሁም የወንዶች 5ሺ ሜትር ፍጻሜ ውድድሮች ተካሂደዋል።



**በዓለም ከ20 ዓመት በታች አትሌቲክስ ቻምፒዮና ኢትዮጵያውያን በርካታ ሜዳሊያዎችን እንደሚያስመዘግቡ ይጠበቃል፣**

ከዓለም ዙሪያ የተሰባሰቡት ከእነዚህ ወጣት አትሌቶች አብዛኛዎቹ በዚህ ውድድር ተካፋይ የሚሆኑት ምናልባትም ለመጀመሪያ ጊዜ ሊሆን ይችላል። በአንጻሩ 15 የሚሆኑት አትሌቶች በማይጠበቅ መልኩ በኦሪጎኑ የዓለም ቻምፒዮና ሃገራቸውን ለመወከል የቻሉ ናቸው። ከእነዚህ መካከል ኢትዮጵያዊት አትሌት ትገኝበታለች። በቻምፒዮናው የሴቶች 3ሺ ሜትር መሰናክል ሃገራቸውን ከወከሉት አትሌቶች መካከል ወጣቷ ሲምቦ አለማየሁ ከሳምንት በኋላ ካሊ ተገኝታለች።

የ17 ዓመቷ ሲምቦ በተያዘው ዓመት ጠንካራ ችሎታዋን ያሳየች ሲሆን፤ በፓሪሱ ዳመንድ ሊግ 9:09.19 የሆነ ሰዓት ማስመዝገቧ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ከ18 ዓመት በታች ቻምፒዮና ላይ ተመሳሳይ ብቃቷን ያስመሰከረችው አትሌቷ በኦሪጎኑ ቻምፒዮና የማጣሪያ ውድድሩን አምስተኛ ሆና ብታጠናቅቅም ለፍጻሜው መብቃት አልቻለችም። ይሁንና አትሌቷ ካላት ልምድ በመነሳት በዚህ ቻምፒዮና ውጤታማ ልትሆን እንደምትችል ይጠበቃል።

ከሲምቦ ባሻገር በውድድሩ ላይ የሚካፈሉ ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ከፍተኛ ፉክክር ከማድረግም ባለፈ እንደለመዱት በርካታ ሜዳሊያዎችን ጠራርገው ይወስዳሉ በሚል ይጠበቃል። ይህም ግምት በየርቀቱ ተሳታፊ የሚሆኑ አትሌቶች ካላቸው ምርጥ ሰዓት በመነሳት ነው። ለአብነት ያህል በ800 ሜትር ወንዶች ኤርሚያስ ግርማ የግሉ ፈጣን ሰዓት 1:44.36 ሲሆን፤ ይህም በርቀቱ ቀዳሚው አትሌት ያደርገዋል። አትሌቱ በ1ሺ500 ሜትርም በተመሳሳይ ፈጣን አትሌት ሲሆን ምርጥ ሰዓቱ 3:36.28 ነው። ይህም አትሌቱ በሁለቱም ርቀት ውጤታማ የመሆን እድሉ የሰፋ እንደሚሆን በግልጽ የሚያመላክት ነው።

የዓለም አትሌቲክስ ፕሬዚዳንት ውድድሩን አስመልክቶ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ላይም ‹‹ይህ ቻምፒዮና አዲስ ብቃት የሚታይበት ነው፤ በመሆኑም ለሁላችንም ትልቅ ውድድር ነው። እአአ በ2002 ጃማይካዊው ዩሴን ቦልት ከዚያ ቀደም ያልታየ ችሎታው ገሃድ የወጣበት ነበር። እአአ 2015 ደግሞ እንደ ሲድኒ ማክላገሊን እና ሞንዶ ዱፕላንቲስ የተባሉትን ወጣት አትሌቶች ችሎታ አሳይቶናል። እነዚሁ አትሌቶች በኦሪጎን ዓለም ቻምፒዮና የክብረወሰን ባለቤት በመሆን ስኬታማ ሆነዋል›› ማለታቸውን ድረገጹ አስነብቧል።

ፕሬዚዳንቱ አስከትለውም የዚህ ውድድር አስፈላጊነት አብዛኛዎቹ አትሌቶች ከወጣትነት ወደ አዋቂነት የሚሸጋገሩበት ዕድል አናሳ በመሆኑ እንደ ድልድይ ለመሆን እንደሆነም ገልጸዋል። በስፖርቱ ብቃት ያላቸውን ወጣት አትሌቶች ከመለየት ባለፈ ማበራታታትም የውድድሩ አንዱ አላማ ነው። የስፖርት ባለሙያዎች በስፖርቱ በሶስትና አራት ዓመት ውስጥ እየታየ ያለውን ለውጥ የሚመለከቱበት መድረክ መሆኑን እንዲሁም በዚህ ውድድር ላይ የሚታዩ ወጣት አትሌቶች በ2024ቱ የፓሪስ ኦሊምፒክ የሚደምቁበት መድረክ እንደሚሆን አመላካች መሆኑን ገልፀዋል።

## አማራ ክልል

ሲኖ ቪዥን ሴራሚክ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

ባሉበት፣

የተቃውሞ አመልካች የኢ.ብ.ክ.መ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ኮርፓሬሽን እና የተቃውሞ ተጠሪ ሲኖ ቪዥን ሴራሚክ ኃ/የተ/የግ/ማህበር መካከል ስለአለው የአፈጻጸም ክስ ክርክር ጉዳይ፤ መከሰስዎን አውቀው ለነሐሴ 17 ቀን 2014 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡30 ሰዓት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል:: ሳትቀርቡ ብትቀሩ ግን ጉዳዩ በሌሉበት ታይቶ በመዝገቡ ላይ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን ፍ/ቤቱ ያሳውቃል፡፡

**የሰ/ሸዋ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት**
**ደ/ብረሃን**

የባለንብረቱ ስም ወንድወሰን ወርቁ እዳለ ሰሌዳ ቁጥር አማ3- 09523አማ የተሽከርካሪው ዓይነት አውቶብስ የተሽከርካሪው የአገልግሎት የህዝብ ማመላለሻ ሞዴል KR-KDH200V-SFMDY የሞተር ቁጥር 2KD-1687824 የሻንሲ ቁጥር KDH200-0089526 የተሽከርካሪ የመጫን አቅም 14ሰው አመታዊ ምርመራ ቀን 26/8/14 ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ተሽከርካሪ ሰሌዳ የጠፋ በመሆኑ ገልፀው በምትኩ እንዲሰጣቸው አመልክተዋል፡፡ ሰሌዳው ወድቆ ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ሪፖርት እንዲያደርግ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑ እንገልፃለን፡፡

**በአብክመ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ የምስ/ጎጃም ዞን መንገድና ትራንስፖርት መምሪያ**

ንብረትነቱ ሰይድ ሀሰን እንድሪስ የሆነ ተሽከርካሪ የፊትና የኋላ ሰሌዳ 01- 35872 አማ መሆኑን ባለቤቱ በቀን 2/07/2014 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ አመልክተዋል፡፡ በዚህም መሰረት ሰሌዳውን ወድቆ ያገኘ ወይን በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ለጽ/ቤቱ ሪፖርት እንዲያደርጉ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑ እንገልፃለን፡፡

**በአብክመ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ የሰሜን ወሎ ዞን መንገድና ትራንስፖርት መምሪያ**

የባለንብረቱ ስም ይዘንጋው ተመቸው አበበ ሰሌዳ ቁጥር አማ -01-58960 የተሽከርካሪው ዓይነት ባለሶስት እግር ተሽከርካሪ ሞዴል re የተሽከርካሪው የአገልግሎት አይነት ለከተማ ታክሲ የሞተር ቁጥር 613004 የሻንሲ ቁጥር 2671792 የተሽከርካሪ የመጫን 3ሰው አመታዊ ምርመራ ቀን 26/2/2012 ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ተሽከርካሪ ሰሌዳ የጠፋ በመሆኑ ገልፀው በምትኩ እንዲሰጣቸው አመልክተዋል፡፡ ሰሌዳው ወድቆ ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ሪፖርት እንዲያደርግ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑ እንገልፃለን፡፡

**በአብክመ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ የምስ/ጎጃም ዞን መንገድና ትራንስፖርት መምሪያ**

## ኦሮሚያ ክልል

የባለንብረቱ ስም አዲሱ በሻዳ ሰሌዳ ቁጥር 3- 61345 ኦሮ የሞተር ቁጥር፡- 8F800248 የሻንሲው ቁጥር፡- LANHCM5B2F0200117 የሆነ ከላይ የተጠቀሰው ባለንብረት ተሽከርካሪ ታርጋ ጠፋብኝ ብለው በ 20/11/2014 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ስለዚህ ታርጋ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ለጽ/ቤቱ ሪፖርት እንዲያድጉ እያስታወቅን በተባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ተለዋጭ ታርጋ የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**የቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ባለስልጣን**

ባለንብረቱ ከፋይ መሸሻ ተሽከርካሪው አይነት ሚኒባስ ሰሌዳ ቁጥር 03-69565 ኦሮ የሻንሲው ቁጥር LH172-1000509 ሞተር ቁጥር 5L-5048379 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ሊብሬ ጠፋብን ብለው በቀን 22/12/2014ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ይህንን ሊብሬ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ለጽ/ቤቱ ሪፖርት እንዲያደርጉ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**የቡራዩ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ባለስልጣን**

የባለንብረቱ ስም ኢብራሂም በለጠ የተሽከርካሪ ዓይነት ባጃጅ ሰሌዳ ቁጥር 1-71463 ኦሮ የሻንሲ ቁጥር 98001 የሞተር ቁጥር 34583 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ20/11/14 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ይህንን ሊብሬ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ለጽ/ቤቱ ሪፖርት እንዲያደርጉ እያሳወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሊብሬ የምንሰጥ መሆኑ እንገልፃለን፡፡

**የምዕራብ ሸዋ ዞን ትራንስፖርት ባለስልጣን**

የባለንብረቱ ስም አቤነዘር ሲሳይ ጠኑ ሰሌዳ ቁጥር 01-11104 ድሬ የተሽከርካሪ ዓይነት ትራይ ሳይክል የሻንሲው ቁጥር፡MC1A4CDE2MA015241 የሞተር ቁጥር፡- D12116065 የባለቤትነት ደብተር ጠፍቶብኛል ብለው በ 08/11/2014 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ሊብሬ /የባለቤትነት ደብተር/ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሊብሬ የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**የድሬዳዋ አስተዳደር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ባለስልጣን**